# የኢፌዲሪ መስኖ ልማት ኮሚሽን የ2013 በጀት ዓመት የመጀመሪያው አጋማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

## መግቢያ

የመስኖ ልማት ኮሚሽን የመስኖውን ዘርፍ ለማሳደግ ብሎም ዘርፉ ለአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የጎላ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2022) በማዘጋጀት ከመቸውም በላቀ ሁኔታ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለአብነት ኮሚሽኑ በእቅድ ዘመኑ የመጀመሪው ዓመት በርካታ የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ፣ በመተግበርና ወደ ልማት በማስገባት የአገሪቱ ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየሠራ ይገኛል፡፡

በዚህም በዋናነት የሚተገበሩ ተግባራትን በተመለከተም በመስኖው ዘርፍ ውጤታማ የጥናት እና የዲዛይን ስራዎች እንዲሁም የግድብና መስኖ አውታሮች ግንባታዎች በተሻለ ጥራት፣ በተቀመጠ ጊዜና በጀት እንዲከናወኑ ተገቢውን ክትትልና ግምገማ የማድረግ፤ አግባብ ካላቸው ሴክተር መ/ቤቶች እና ክልል መንግስታት ስር ካሉ ዘርፎች ጋር በቅንጅት የመስራት፣ በዘርፉ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ያለውን አሰራር ውጤታማ እንዲያደርጉ፣ ተጠንተው የቆዩ የመሰረተ ልማት ጥናቶች እንዲከለሱና ለግንባታ ዝግጁ እንዲሆኑ፣ ያለቁና በስራ ላይ ያሉ መሰረተ ልማቶች ዘላቂ አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት ሁኔታ እንዲተዳደሩ ማድረግ፤ ፕሮጀክቶች በማህበረሰብ እና በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ተፅእኖዎች እንዳይኖሩ ወይም እንዲቀንሱ አስቀድሞ ተገቢ የሆኑ የችግር መፍቻ መፍትሄዎች የማስቀመጥ እርምጃዎች መውሰድና በግንባታ ወቅትም ክትትል ማድረግ፣ የተቋሙ አደረጃጀትም ሆነ በውስጡ ያሉ ባለሙያዎች አቅም እንዲጎለብት በማድረግ እና ውጤታማ የስራ አመራርና የድጋፍ አሰጣጥ ሂደቶችን በመዘርጋት የ2013 በጀት አመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም መሠረት የኮሚሽኑ የ2013 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከዚህ በታች እንደተመለከተው የቀረበ ሲሆን በሪፖርቱ የተካተቱትም በዋናነት የመስኖ ግድብ ግንባታ፣ የመስኖ መሬት ዝግጅትና የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ናቸው፡፡

# **የመስኖ ልማት ኮሚሽን** የ2013 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

የመስኖ ልማት ኮሚሽን በህግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው በ2013 በጀት ዓመት ወይም በአራተኛው የፕሮግራም በጀት ዘመን (ከ2013-2015) ሁለት ፕሮግራሞችን በማዋቀርና የፕሮግራሞቹንም አፈጻጸም ስኬታማ ለማድረግ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል። በዚሁ መሠረት የፕሮግራሞቹ ዝርዝር ዓላማ፣ በ2013 በጀት አመት በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የታቀዱና የተከናወኑ ቁልፍ እና አበይት ተግባራት ከማጠቃለያው ቀጥሎ ቀርቧል።

የመስኖ ልማት ኮሚሽን በሁለት ፕሮግራሞች የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም

ፕሮግራም አንድ፡ የሥራ አመራርና ድጋፍ ፕሮግራም

ፕሮግራም ሁለት፡ የመስኖ ልማት ፕሮግራም ናቸው።

ዓላማ፡- ከ2013 እስከ 2015 ዓ. ም ባለው ጊዜ ውስጥ የመካከለኛና ሰፋፊ መስኖ ልማትን ከ490,000 ሄክታር ወደ 535,225 ሄክታር ማድረስና (መነሻው ተስተካክሏል) በዚህም የሴቶችን ፍትሃዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ።

## ክፍል አንድ፡- የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ስድስት ወራት የዋና ግቦች ዕቅድ አፈጻጸም ማጠቃለያ

ከላይ ከቀረቡት ሁለት ፕሮግራሞች ውስጥ በአንዱ አላማ አስፈፃሚ ፕሮግራም አማካኝነት የተለያዩ የመስኖና ድሬኔጅ ልማት ፕሮጀክቶች የተከናወኑ ሲሆን የነዚህም ማጠቃለያ ቀጥሎ ቀርቧል።

**መስኖና ድሬኔጅ ልማት፡-** በበጀት ዓመቱ ውስጥ የ13 የመስኖ ልማት ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ሰነዶች ዝግጅት(9 የጥናት ዲዛይንና የክለሳ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ)፣ የ23 የመስኖ ልማት ግንባታ፣ 3 የመስኖ ጥገና፣ አንድ የመስኖ ቴክኖሎጂና አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶችና የተማሩ ወጣቶች መስኖ ልማት ፕሮግራም ታቅደው በመካሄድ ላይ የሚገኙ ሲሆን  የበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸምም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

**ግድብና የውሃ ውቅሮች ግንባታ**፡- በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ የሶስት ግድቦች ግንባታን (አማራ ክልል መገጭ ግድብ ግንባታ (10981 ሄ/ር)፣ ኦሮሚያ ክልል አርጆ ደዴሳ ግድብ ግንባታ (80000 ሄ/ር) እና ትግራይ ክልል ዛሪማ ሜይ ዴይ ግድብ ግንባታ (40000 ሄ/ር)) እያንዳንዳቸው 7.7 በመቶ፣ 5.13 በመቶ እና 5.3 በመቶ ሲከናወኑ የጊዳቦ ግድብ ግንባታ አካል የሆነው የዋና ቦይ ግንባታ የ6 ወራት አፈጻጸም 103 በመቶ ሆኗል።

በበጀት ዓመቱ ውስጥ **በመካሄድ ላይ ያሉ ነባር የግንባታ ፕሮጀክቶች**

**መስኖ መሬት ዝግጅት፡-**

- በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በመካሄድ ላይ የሚገኙ የሶስት ፕሮጀክቶች የግማሽ ዓመት አፈጻጸም በተመለከተ የላይኛው ርብ መስኖ ልማት ግንባታ(6002 ሄክታር) 27.1 በመቶ እና የአጂማ ጫጫ ግድብ ግንባታ (ሎት 3) (7000 ሄ/ር) 114.25 በመቶ ሲከናወኑ የርብ መስኖ አውታር ግንባታ (3471 ሄ/ር) አልተከናወነም፡፡
- በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በመካሄድ ላይ የሚገኙ የሶስት ፕሮጀክቶች የግማሽ ዓመት አፈጻጸም በተመለከተ የወልመል መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሎት 1 እና ሎት 2 እያንዳንዳቸውን 51.85 በመቶ እና 13.6 በመቶ፣ የጨልጨል መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሎት 1 እና ሎት 2 እያንዳንዳቸውን 20.8 በመቶ እና 16.8 በመቶ፣ የላይኛው ጉደርን መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሎት 1 እና ሎት 2 እያንዳንዳቸውን 26.98 በመቶ እና 14.9 በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡
- በትግራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በመካሄድ ላይ የሚገኘው የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክትና እና በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በመካሄድ ላይ የሚገኘው ዱብቲ ዳይክና መስኖ አውታር ጥገና ፕሮጀክቶች አልተከናወኑም፡፡

**ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን፡-**

የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች የሩብ ዓመቱን አፈጻጸም በተመለከተ ትርካን ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክትን 33.3 በመቶ፣ ሴን ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክትን 75 በመቶ፣ ጊሎ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክትን 24.3 በመቶ፣ በለስ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክትን 33.3 በመቶ ሲከናወኑ የሚሌ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት የተመረጠው ቦታ በክልሉ ባለመፈለጉ አልተከናወነም፡፡ በሌላ በኩል የሽንሌ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክትን ከዕቅድ ውጪ 4 በመቶ እና የቦረና ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክትን 3 በመቶ ማከናወን የተቻለ ሲሆን ሌሎች አዲስ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ላይ የሚገኙ በመሆናቸው አልተከናወኑም፡፡

**በመጀመሪያው ስድስት ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል ማጠቃለያ**

| የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ከ18-35 ዓመት** | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | |
| ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ጠ. ድምር |
| **2,763** | 576 | 3,339 | 1,404 | 102 | 1,506 | 4,166 | 678 | 4,845 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለበጀት ዓመቱ ለተቋሙ መደበኛ ስራዎች እና ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ብር 16.098 ቢሊዮን ብር የታቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በመጀመሪው 6 ወራት ብር 4.776.566 ቢሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ ታቅዶ የዕቅዱ 27.76 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

በግማሽ ዓመቱ ከተደረገው ወጪ

- ❖ ለመስኖ ልማት ፕሮግራም
  - ለጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ንዑስ ፕሮግራምና ለወጣቶች መስኖ ልማት ፕሮግራም 1,315.85 ሚሊዮን ብር፣ እንዲሁም ለግንባታ ክትትል ብር 46,740.16፣
  - በመደበኛ በጀት ለሚካሄዱ ለሶስት ንዑሳን ፕሮግራሞች 573,103.62 ብር (ለመስኖ መሠረተ ልማት ንዑስ ፕሮግራም 296,895.95 ብር፣ ለመስኖ ቴክኖሎጂና አቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም 275,,041.87 ብር እና ለአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ንዑስ ፕሮግራም 1,165.80 ብር) እንዲሁም
- ❖ ለስራ አመራርና ድጋፍ ፕሮግራም 9.3 ሚሊዮን ብር ሥራ ላይ ማዋል ተችሏል።
- ❖ በተጨማሪ ለኮቪድ 19 መከላከያ እንዲውል ከተመደበው 672 ሚሊዮን ብር ውስጥ 179.32 ሚሊዮን ብር (26.7 በሙቶ) ወጪ ሆኖ ስራ ላይ ውሏል።

የፋይናንስ አጠቃቀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ዋናው ምክንያት የፊዚካል ሥራዎች አፈጻጸም ዝቅተኛ በመሆኑና ከገንዘብ ሚኒስቴር በጀት በወቅቱ ባለመለቀቁ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው 6 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ዝርዝር ሪፖርት

በዚህ ስር በ6 ወራት ታቅደው የተተገበሩ የመደበኛ ስራዎችና ካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በዝርዝር ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ቀርቧል፡፡

## *I. በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት*

- የዘርፉን የ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም በማኔጅመንት አባላትና ሰራተኛው በጋራ ግምገማ ካካሄደ በኋላ የዘርፉን የ2013 በጀት አመት አመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት በማኔጅመንት አባላትና ሁሉም ፈፃሚ ባለበት በጋራ በመገምገምና ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻው የበጀት አመቱ የድርጊት መርሀ ግብር እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
- ለአገልግሎት ፈላጊ ህብረተሰብ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል በመልካም አስተዳደር ዙሪያ በ2012 በጀት ዓመት የታዩ ችግሮችን በመለየትና ከተገልጋዮች የተገኙ ግብዓቶች በመነሳት የ2013 በጀት ዓመት የመልካም አስተዳደርና ከለውጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች ዕቅድ በማዘጋጀትና ሠራተኛው ተወያይቶበት ግንዛቤ እንዲጨብጥ ተደርጓል፡፡
- በተቋሙ ጠንካራ ቁመና ያለው የለውጥ ሰራዊት መገንባት እንዲቻል ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ተከናውኗል፡፡

- በተቋሙ የውጤት ተኮር እቅድን በየዳይሬክቶሬቱ ላሉ ሠራተኞች ሳምታዊ፣ ወርሃዊና አመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት በአፈጻጸሙ ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡ በዚህም የሚታዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶችን በመለየት ጥንካሬዎች ይበልጥ ተጠናክረው የሚሄዱበትን እና ችግሮችም እንዲቀረፉ ተደርጓል፡፡

## II. በትግበራ ምዕራፍ የተከናወኑ

### ሀ የቁልፍ ተግባር አፈጻጸም

➢ **የበላይና መካከለኛ አመራር ሁኔታ፡-**

- የበላይ አመራሩ የ2013 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን በመገምገም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚ ሠራተኛው ግንዛቤ በመያዝ ለአፈጻጸሙ ዝግጁ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡
- ከፍተኛ አመራሩ ከእቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ክትትል ጀምሮ በተቋሙ የሚከናወኑ የለውጥና መልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም ሪፖርት የሚገመግምና አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ሲሆን በዝግጅት ምዕራፍ ወቅት የ2012 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እና የ2013 በጀት ዓመት እቅድ ዝግጅት በተለይ የተቋም ለውጥ፤ የለውጥ ሰራዊት ግንባታ፣ የመልካም አስተዳደርና ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሎችን መሰረት ያደረገ የተቋሙን አመራርና ሰራተኞች ማዕከል ያደረገ ግምገማዊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

➢ ሠራተኛውን በተመለከተ፡- የስራ ሰዓት የማክበር፣ የእቅድ አፈፃፀም ግምገማዎች ላይ ተሳትፎ የማድረግ፣ አዳዲስ ሃሳቦችን ለመቀበል ዝግጁ መሆኑና ካይዘን ለመተግበር ተነሳሽነት ማሳየቱ መልካም ጅምር ላይ መሆኑ በበጎ ጎኑ ታይቷል::

➢ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ በለውጥና መልካም አስተዳደር ረገድ በተከናወኑ ሥራዎች አማካይነት የአብዛኛው ሠራተኛ አመለካከት ላይ ለውጦች መታየታቸውና በዚህም የሠራተኛውን የቡድን ስሜት በማሳደግ በስራ አካባቢ የሚከሰቱ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፣

➢ የለዉጥ ሰራዊት ግንባታ አፈፃፀም በተመለከተ፡- በበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት ውስጥ በተደረጉ የሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የሠራተኛውን ግንዛቤ ከመፍጠር አንስቶ ጠንካራ የለውጥ ሰራዊት መገንባት እንዲቻል ወቅታዊ ውይይት ማድረግ፡ ተልዕኮን መፈጸምና እርስ በእርስ በመማማር በሂደት የአመለካከት፣ የአሰራር፣ የአደረጃጀት እንዲሁም የእውቀት ክፍተቶች በመሙላት ረገድ መልካም ጅማሮዎች ታይተዋል፡፡ በተቋሙ በሚደረግ ክትትልና እገዛ ሠራተኛው በራሱ ያከናወናቸውን ስራዎች መገምገምና ያልተሰሩትን ከነምክንያታቸው መረዳት እና በስራ ቦታ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በዉይይት ለመፍታት፣ ስራን በእቅድ በማከናወን እና አፈጻጸምን በመገምገም ረገድ አጥጋቢ ሥራዎች (በቀጣይ የበለጠ መስራቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) ተሠርተዋል፡፡

- መንግስት ለሴቶች የሰጠውን ማበረታቻ/Affarmative action/ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጥር በመፈጸም፣ በስልጠና በማብቃትና ወደ አመራር የማምጣት ስራ ላይ አመራሩ ድጋፍ አድርጓል፡፡
- የመልካም አስተዳደርን በተመለከተ፡- በተቋሙ ያልተፈቱ የሠራተኞችም ሆነ ሌሎች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት ተገቢው ምላሽ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡
- **የቅሬታና አቤቱታ ስርዓት ትግበራ፡-** በተቋሙ ውስጥ ለሚገለገሉ ባለድርሻ አካላት እና ለተቋሙ ሠራተኞች ተቋሙ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች እና አሰራሮች ዙሪያ ቅሬታም ሆነ አስተያየት ሲኖራቸው ለአስተያየት መቀበያ የሚሆኑ የሐሳብ መስጫ ሳጥኖች በተመረጡ ቦታዎች እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡
- **የኪራይ ሰብሳቢነትን አመለካከትና ተግባር ከመዋጋት አንጻር**
  - በሩብ ዓመቱ ውስጥ የቋሚ እና አላቂ ንብረቶች የመንግስት የግዢ ደንብና መመሪያን ተከትሎ እንዲከናወን ከየስራ ክፍሉ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን የተሽከረካሪዎች አጠቃቀምን በተመለከተም አንድ ተሽከረካሪ በኃላፊነት ለአንድ አሽከርካሪ በመስጠት ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡
  - ሠራተኞች ለሥራ የሚጠቀሙባቸውን የመንግስት ንብረቶችና ሌሎች አገልግሎቶች (መብራት፣ ውሃ፣ ወዘተ) በጥንቃቄና በቁጠባ እንዲጠቀሙ ተገቢውን ምክር የመስጠትና የግንዛቤ ማስጨባጫ ሥራ ተሰርቷል፡፡
  - ሠራተኛው የመንግሰትን የስራ ሰአት አክብሮ ቢሮ እንዲገባ፣የስራ ሰአቱን ለመንግስት ስራ አገልግሎት እንዲያውል እየተደረገ ይገኛል፡፡
- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንጻር፡- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትስስርና ቅንጅትን አጠናክሮ ለመቀጠል በሚያስችልበት ሁኔታ ላይ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የደንበኞች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ተቋሙ ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት አድርጓል፡፡

# ለ አበይት ተግባራት

## ፕሮግራም አንድ፡ ሥራ አመራርና ድጋፍ አስተዳደር

**ዓላማ፡-** ለዓላማ ፈጻሚ ፕሮግራም ስትራቴጂክ አመራርና ቀልጣፋ የድጋፍ አገልግሎት በመስጠት ተቋሙ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ማስቻል፡፡

በፕሮግራም አንድ የታቀፉት ድጋፍ ሰጭ ዳይሬክቶሬቶች የፋይናንስ አስተዳደር፣ የዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ፣ ንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት፣ የውስጥ ኦዲት፣ የህግ አገልግሎት፣ የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት፣ የኮሙኒኬሽንና የውጪ ግንኙነት፣ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች እና

የግዥና ኮንትራት አስተዳደር ሲሆኑ የእነዚህ ድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎች የግማሽ ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀም በጥቅል ሲታይ በአጥጋቢ ሁኔታ ተከናውነዋል፡- ዝርዝር አፈጻጸሙም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 1.1 ግዥና ኮንትራት አስተዳደር

- የጨረታ ሰነዶችን በጥንቃቄ ማዘጋጀት፣ መስፈርት ላሚሉ ገዥዎች እየመዘገበ መሸጥና እንዳስፈላጊነቱ ማብራሪያ ወይም የጨረታ ሰነድ ማሻሻያ በጽሁፍ መስጠት 100%፣
- የጨረታ መዝጊያና መክፈቻ ሂደቶችን በበላይነት መምራት 100%፣
- የጨረታ ግምገማዎችን ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ፤ የጨረታውን ውጤት ለተጫራቾች ማሳወቅና ቅሬታዎች ከቀረቡም በአግባቡ መልስ መስጠት 100%፣
- ዋና የውል ሰነዶችንና የተጨማሪ ውል ሰነዶችን በማዘጋጀት የበላይ አመራሩ እና ተቋራጩ/ አማካሪው እንዲፈራረሙ ማድረግ 100%፣
- የግንባታ/ የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በሳይቶች በመገኘትና በሦስትዮሽ መድረክ መገምገም 100%፣
- የጊዜ ማራዘሚያ፣ የተጨማሪ ሥራ፣ የለውጥ ሥራ እና የግንባታ ዋጋ ለውጥ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ተገቢውን ምላሽ መስጠት100%፣
- የመጀመሪያ ሩብ ፤ግማሽ፤ የስራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በወቅቱ አዘጋጅቶ ማቅረብ ማቅረብ በዕቅዱ መሠረት ተከናዉኗል፡፡

### ታቅደው ያልተከናወኑ ስራዎች

- የክፍያ ሰነዶችን መርምሮ ማጽደቅ፣
- ጊዜያዊና የመጨረሻ ርክክብ ማድረግ፣
- የመገጭ ሰራባ ፕሮጀክት ርክክብ፣

➢ የግዥና ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሩብ ዓመቱ አፈጻጸም 76.25 በመቶ ነው፡፡

## 1.2 ፋይናንስ አስተዳደር

- ከገ/ሚ/ር በወቅቱ ተጠይቆ የሚፈቀድ የመደበኛና የካፒታል የጥሬ ገንዘብ ፍላጐት፤ ተፈቅዶ የመጣውን የመደበኛና የካፒታል በጀት ዝርዝር በገቢ መመዝገብ በየወሩ የተዘጋጀ የመንግሥት በጀት አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረብ100%፣
- ከገ/ሚ/ር ተፈቅዶ የመጣውን የመደበኛና የካፒታል በጀት ዝርዝር በገቢ መዝገብ መያዝ 100%፣
- ከበጀት አንፃር በወጪ መዝገብ የሚመዘገብ የተረጋገጠ ከመንግሥት የተገኘ መደበኛና የካፒታል በጀት 100%፣

- ከመንግሥት የመደበኛና የካፒታል በጀት የሚገኙ ተረጋግጠው የሚመዘገቡ ወጪዎች 100%፣
- የቋሚና የኮንትራት ሠራተኞችን ደመወዝና አበል ክፍያ መፈፀም እንዲሁም የተለየዩ ተቀናናሾችን ለሚመለከታቸው አካላት ገቢ ማድረግ 100%፣
- ለዕቃዎችና ለአገልግሎቶች ግዥ፣ ለኮንሰልታንቶች፣ ለግንባታ፣ ለውሎ አበልና ለሥራ ማሰኬጃ፣ ለካሳ፣ ለክልሎች፣ በባንክ የሚፈፀሙ እንዲሁም የሚወራረዱ ክፍያዎች100%
- ከሳጥን የሚከፈል እንዲሁም በሳጥን የሚገኝ የተመዛዘነ ከብር 5,000.00 በታች የሆኑ የተለያዩ ክፍያዎችን መፈፀም 100%፣
- በቅድሚያ ለተከፈለ የውሎ አበልና የሥራ ማሰኬጃ የተወራረደ ሂሣብ ሪፖርት ማዘጋጀት 100%፣
- በጄነራል ሰብሲደሪ ሌዠር ላይ የሚመዘገብ የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃላይ እንቅስቃሴ ሪፖርት ማዘጋጀት 100%፣
- ተገቢው የሂሣብ ሥራዎች እና ዕርምት ተከናውኖባቸው የተጠናቀቁ ሰነዶችን አደራጅቶ በመያዝ ለኦዲተሮችም ሆነ ለተለያዩ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ተገልጋዮች ዝግጁ ማድረግ100%፣
- በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች የቀረቡ የኦዲት ግኝቶች ላይ አሰፈላጊውን የእርምትና የክትትል ሥራ ማከናወን 50%፣
- ቋሚ የቢሮ ዕቃዎችና የፅህፈት መሳሪያዎች ጥቅል ግዥ የክትትል ስራ፣
- በግዥ ኤጀንሲ በኩል የሚገዙትን ግዥዎች ክትትል ማድረግ 50% ተከናውኗል፡፡
- ከሂሣብ መዝገብና ከሌዠር በመነሳት እንዲሁም የገ/ሚ/ር ባወጣው መመሪያ መሠረት ያለፈውን ወር ሂሣብ በተከታዩ ወር በ15 ቀናት በማዘጋጀት የሚቀርብ አጠቃላይ የመ/ቤቱ ሂሣብ ሪፖርት **66.67** % ተከናውኗል፡፡

***ታቀደው ያልተከናወኑ***

- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚካሄድን የበጀት ዝውውር በየአርዕስቱ ምዝገባ ማከናወን፣
- ከሂሣብ መዝገብና ከሌዠር በመነሳት እንዲሁም የገ/ሚ/ር ባወጣው መመሪያ መሠረት ያለፈውን ወር ሂሣብ በተከታዩ ወር በ15 ቀናት በማዘጋጀት የሚቀርብ አጠቃላይ የመ/ቤቱ ሂሣብ ሪፖርት፣

➢ የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሩብ ዓመቱ አፈጻጸም 75.45 በመቶ ነው፡፡

## 1.3 ዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ

***ዕቅድ ዝግጅት***

- የኮሚሽኑ መ/ቤት የ2013 በጀት አመት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡

- በዕቅድ አዘገጃጀት ሂደት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች መካተታቸውን የማረጋገጥ ስራ ተከናውኗል፡፡

**ክትትል፣ግምገማና ሪፖርት ዝግጅት**

- የ2013 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ባለድርሻ አካላት በሚፈልጉት ፎርማት መሠረት አዘጋጅቶ ለመላክ በታቀደው መሠረት ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ከተገመገሙ በኂላ ለሚመለከታቸው አካላት ተልከዋል፡፡
- በበጀት ዓመቱ 6 ወራት ውስጥ የ4 ሰነዶች ወይም ሪፖርቶች ዝግጅት ጥራትና ወቅታዊነት አስመልክቶ ግብረ መልስ ለመስጠት በታቀደው መሠረት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ግብረ መልስ ለሥራ ክፍሎች ተሰጥቷል፡፡
- በመጀመሪያው 6 ወራት በሪፖርት አዘገጃጀት ሂደት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች መካተታቸውን የማረጋገጥ ስራ በ4 ሰነዶች ላይ ለማከናወን በታቀደው መሠረት ላይ ተከናውኗል፡፡
- የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በመስክ ላይ ክትትል ማድረግን በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን፣ አሳግርት ወረዳ በመካሄድ ላይ ያለውን የአጂማ ጫጫን ሎት3 የግድብ ግንባታ እንቅስቃሴ የማየትና በግንባታው ላይ ለወጣቶች እየተደረገ ያለውን የሥራ ዕድል ፈጠራ ከፕሮጀክቱ ማናጀርና ሌሎች ሃላፊዎች እንዲሁም ከወረዳው አስተዳደር ጋር ድጋፉ ተጠናክሮ መቀጠል በሚችልበት ሁኔታ ላይ ውይይቶች ማድረግ ተችሏል፡፡

**ለመረጃ ፈላጊዎች መረጃ መስጠትን በተመለከተ፡-**

- ወቅታዊ የዕቅድ፣ክትትልና ግምገማ መረጃዎችን በማደራጀትና ለተጠቃሚዎች ለመስጠት በታቀደው መሠረት አገልግሎት ለማግኘት ደብዳቤ አጽፈው ለመጡና መረጃው እንዲሰጥ በኃላፊዎች ታዞ ለዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ደብዳቤው ሲመራ መረጃውን ለተለያዩ መ/ቤቶች መስጠት ተችሏል፡፡

**በጀት ዝግጅትና አስተዳደር**

የበጀት ዓመቱ የበጀት ፍላጎት ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚ/ር ቀርቦ የተፈቀደ ሲሆን የበጀት አጠቃቀሙንም በየወሩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሪፖርት የማዘጋጀት፣ የውሎ አበል ወጪን ለመቆጣጠር እንዲቻል ለኮሚሽኑ መደበኛ ሥራዎች በጥቅል የተፈቀደውን ለየሥራ ክፍሎች በመመደብና ወጪውንም በየጊዜው በመመዝገብ ክትትል የማድረግ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

- የዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም 89.7 በመቶ ነው፡፡

## 1.4 የኮሚኒኬሽንና ውጭ ግንኙነት

- *በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ታቅደው የተከናወኑ ተግባራት*

- የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን ተጠቅሞ መረጃ ከማሰራጨት አኳያ
  - በቁጥር 1 ጋዜጣዊ መግለጫ /ፕሬስ ኮንፈረንስ ለማስተባበር ታቅዶ 1(00%) ተከናውነዋል፡፡
  - በቁጥር 12 የዜና መግለጫ/ ፕሬስ ሪሊዝ ማዘጋጀትና ለሚዲያ መላክ ታቅዶ 13(108%) ተከናውነዋል፡፡
  - በቁጥር 12 ቃለምልልስ ለማካሄድ ታቅዶ 14 (117%) ተከናውነዋል፡፡
  - በቁጥር 120 ጊዜ የሃገር ውስጥና የውጭ  ፕሬስና/ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ሞኒተር ማድረግ ታቅዶ  (100%) ተከናውነዋል፡፡

- *የህትመት ስራዎች*
  - በቁጥር 1 ጊዜ መልዕክት መቅረፅና ማስተላለፍ ታቅዶ 1 (100%) ተከናውነዋል፡፡
  - በቁጥር 100 ቡክሌት ማዘጋጀትና ማሰራጨት  ታቅዶ አልተከናወነም ፡፡
  - በቁጥር 200 ብሮሽር ማዘጋጀትና ማሰራጨት  ታቅዶ  173 (86.5%) ተከናውነዋል፡፡
  - በቁጥር 2 አርቲክሎችን ማዘጋጀትና መጠቀም ታቅዶ 2(100%) ተከናውነዋል፡፡
  - በቁጥር 200 በራሪ ወረቀቶችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት  ታቅዶ 120 (60%) ተከናውነዋል፡፡

- *ሁነት ማዘጋጀትና መድረክ መምራት*

- *በቁጥር 2 ሁነት ማዘጋጀትና መድረክ መምራት ታቅዶ 2(100%) ተከናውነዋል፡፡*
  - በቁጥር አንድ የሰንደቅ አላማ ቀን ማክበር ታቅዶ 1(100%)  ተከናውነዋል፡፡
  - በቁጥር 1 የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀንና ወቅታዊ ሁኔታ የምክክር መድረክ መምራትና ማስተባበር ታቅዶ *(100%) ተከናውነዋል* ፡፡

- *መረጃን በወቅቱና በአግባቡ ለመረጃ ፈላጊና ለሚመለከተው አካል መስጠት*
  - በቁጥር አንድ ጊዜ የመረጃ ማዕከላት ማጠናከር ታቅዶ 1 /100%/ ተከናውነዋል::
  - በቁጥር 12 መረጃ ፈልጎ በአካል ለሚመጣ ቶሎ መረጃ መስጠት ታቅዶ 15 (125%) ተከናውነዋል::

- የውስጥ ኮምዩኒኬሽን ማጠናከር

- በቁጥር 1 ጊዜ የተቋሙን ሠራተኞች በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ማወያየት ታቅዶ 1 /100%/ ተከናውነዋል::

- በተቋሙ ዌብ ሳይት ፌስ ቡክ ላይ በቁጥር 12 ወቅታዊ መረጃ መጫን ታቅዶ 16/133%/ ተከናውነዋል::

- በዳይሬክቶሬቱ ፌስቡክ ላይ በቁጥር 10 መረጃ መጫን ታቅዶ 14/140%/ ተከናውነዋል::

- *በቁጥር ሁለቱ  የመልካም ምኞት መግለጫ ካርድ ዝግጅትና ስርጭት ታቅዶ ህትመት አልተከናወነም፡፡ ነገር ግን ፖስት ካርዱ ተዘጋጅቶ በዌብ ሳይት /በኮሚሽኑና በዳይሬክቶሬቱ ፌስ ቡክ ላይ ተጭነዋል::*
- *በቁጥር ሶስት የሚዲያዎች የልማት ቦታ ጉብኝት ማስተባበር ታቅዶ* 1 /33%/ ተከናውነዋል፡፡
  - ከኢ.ቢ.ሲ. ቴሌቭ¡ንና የፕረስ  ጋዜጠኞች  ፕሮጀክቶችን ጉብኝተው ዜና ተዘጋጅተዋል ::
- *በቁጥር 3 ስልጠና ማስተባበር ታቅዶ አልተከናወነም::*
- *በቁጥር 12 መረጃዎች በፊልምና በፎቶ ቀሪጸ መያዝ ታቅዶ 14 /117%/ ተከናውነዋል::*
  - *በቁጥር 6 መረጃዎችን በፎቶ ቀርፆ መያዝ ታቅዶ 7(116%) ተከናውነዋል፡፡*
  - *በቁጥር 6 መረጃዎችን በቪዲዮ ቀረፃ መያዝ ታቅዶ 7/116%/ ተከናውነዋል፡፡*
- *በቁጥር 1 ከፍተኛ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ ለመቅጠር ታቅዶ* 2 /200%/ተከናወነዋል፡፡
- *ታቅደው ያልተከናወኑ ተግባራት*
  - *የሚዲያዎች የልማት ቦታ ጉብኝት በመኪና ችግር ምክኒያት አልተከናወነም፡፡*
  - በቁጥር  100 ቡክሌት  *ማዘጋጀትና ማሰራጨት  ታቅዶ* በመረጃ ዕጥረት  ምክንያት አልተከናወነም፡፡
- *ከዕቅድ ውጭ የተከናወኑ ተግባራት*
  - *ዝዋይ- መቂ መስኖ ልማት ፕሮጀክት፣ የደርባ ከተማ ችግኝ ተከላና የላይኛው ጉደር፣ አጂማ - ጫጫ እና ጊዳቦ  መስኖ ልማት  ፕሮጀክቶች  አጭር ቪድዮ ተዘጋጅቶ  በፌስ ቡክ ተጭነዋል፡፡*

➢ የኮሚኒኬሽንና ውጭ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የሩብ ዓመቱ አፈጻጸም 82.6 በመቶ ነው፡፡

## 1.5 የንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት

- በግዥም ሆነ በእርዳታ የመጡ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአግባቡ ተመዝግበዉ የስርጭት ስራዎች እንዲከናወኑ ተደርጓል፡፡
- የተሽከሪካርዎችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ ጥገና የሚያስፈልጋቸዉን ተሽከርካሪዎች የማስጠገን ስራ ተከናዉናል፣
- በአለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተዉ Covid-19 ወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችለዉን የምርት መቀነስ እና ምርታማነትን ለማሳደግ ሲባል ለክልሎች ፓምፕ እንዲገዛ መንግስት በጀት በመደበዉ መሰረት ለትግራይ፣ ለኦሮሚያ፣ ለሱማሌ፣ ለደቡብ፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ለአማራ፣ ለሃረርና ድሬዳዋ ክልሎች 5367 ፓምፖች ከነሆዞቻቸዉ ተገዝተው ስርጭት ተደርጓል፡፡
- በማደያ ላይ ያለዉን ነዳጅ በተለያዩ ጊዜ ለሰርቪስና ለመስክ የሚወጡ ነዳጅና ዘይት አጠቃቀም ላይ ክትትል ስራ ተደርጓል፣
- .ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በክፍፍል የተሰጠን 34 ተሽከርካሪዎች ሊቢሬአቸዉን ወደ ተቋማችን እንዲዛወር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣

- አስራ ስምንት የገመድ አልባ ስልኮች ግዥ ተፈፅሟል፣
- አጠቃላይ የተሽከርካርዎች እስፐር ፓርት ግዥ በስስተም ተጠይቆ ግዥ በመፈፀም ላይ ይገኛል፣
- የስልክ፣ የኢንተርነት፣ የዉሃና የመብራት አገልግሎት ክፍያ በተመለከተ በ2012 በጀት ዓመት ሳይከፈል የመጣዉን ዉዝፍ ክፍያ ለ4 መስሪያ በቶች ተከፋፍሎ 'የደረሰን 270.046.02 ክፍያ ተፈጽሟል፣
- የቢሮዉ የአገልግሎት ክፈያ ማለትም የዉሃ፣ የመብራት፣ የስልክና የኢንተርኔት ክፍያ ተፈጽሟል፣
- የ39 ተሽከረካሪዎች የመድህን ዋስትና ኢንሹራንስ ክፍያ ብር 528.449.80 ክፍያ ተፈፅሟል፣
- የስምሪትና የነዳጅ ስርጭት አጠቃቀም በተመለከተ ናፍታ በ6 ወር ዉስጥ 420,000 እና ቤንዚን 68,896 ብር ስራ ላይ ዉሏል፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተካሂዷል

***ዕቅድ ተይዞ ያልተከናወነ፡-*** የመኪና ታርጋ ቁጥር ማዉጣት

የንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የ6 ወራት አፈጻጸም 74.1 በመቶ ነው፡፡

## የህግ አገልግሎት

- በ 6 ወራት ውስጥ 36 የውል ስምምነት ሰነዶች ተረጋግጠዋል፣
- በ 6 ወር ውስጥ 46 የሕግ አስተያየቶችን ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎችና የሥራ ክፍሎች ተሰጥተዋል፣

ኮሚሽኑ በተከሰሰባቸውና በከሰሰባቸው የፍትሐብሔር መዝገቦች ዙሪያ

- በኢትዮ ናይል የመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አማካኝነት እየተከናወነ ባለው የተፋሰስ እንክብካቤ ሥራ ጋር በተያያዘ በአካባቢው በሚገኝ ወንዝ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው አርሶ አደሮች በጠቅላላ የገንዘብ መጠናቸው ብር 1,869,264.87 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አራት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) በሆነ አስራ ሶስት መዝገቦች በኮሚሽኑ ላይ የካሳ ክፍያ ክስ አቅርበውና ዳይሬክቶሬታችንም መልስ ሰጥቶ ጉዳዩ በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛል፣
- ከአርጆ ደዴሳ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ በ2 መዝገቦች ለተመሰረተብን ክስ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነፃ ተሰናብተን መዝገቡ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነቀምት ተዘዋዋሪ ችሎት ይግባኝ ተጠይቆበት በጊዜ ቀጠሮ ላይ ይገኛል፣

- በድምሩ  የብር 2,613,975 .95 (ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አምስት ከዘጠና አምስት ሳንቲም) ውል ከኮሚሽኑ ጋር የነበራቸው ሁለት የሥራ ተቋራጮች በገቡት የውል ግዴታ መሠረት ግዴታቸውን ሊወጡ ባለመቻላቸው  የወሰዱትን ከላይ የተጠቀሰውን የቅድመ ክፍያ ብር ተመላሽ እንዲደደደርጉ የክስ አቤቱታ አቅርበን እና ክርክር ተደርጐ በሁለቱም መዝገቦች ከላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሥራ ተቋራጮቹ እንዲከፍሉ አስወስነን እና የአፈፃፀም መዝገብ ከፍተን በቀጠሮ ላይ ይገኛል፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት (ሰሜን ገንደር) በመታየት ላይ ያሉ መዝገቦች ብዛት 4 ሲሆን መዝገቦቹ የያዙት ( ክስ የቀረበበት) የገንዘብ መጠን 13,700,946.21 (አስራ ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርበ  ስድስት ብር ከሃያአንድ ሳንቲም ) ለብይን በቀጠሮ ላይ ይገኛል፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አራት መዝገብ በይግባኝ እና በቀጥታ ክስ በመታይት ላይ  ይገኛል፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 16 የፍ/ብሔር መዝገቦች በመታየት ላይ የሚገኙ ሲሆን መዝገቦች የያዙት (ክስ የቀረበበት) የገንዘብ መጠን 3,603,000  በተለያየ ደረጃ በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፣
- ከቆጋ መስኖ ግድብ ጋር በተያያዘ ምትክ መሬት በወቅቱ አልተሰጠንም በማለት ብዛታቸው 21 የሆኑ አርሶ አደሮች የብር 35,623,596(ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ስድስት ብር) ክስ በክልሉ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ቢሮ እና በወረዳው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ላይ ክስ መስረተው ተከሳሾች የግድቡ ባለቤት ጣልቃ ይግባልን በሚል በመጠየቃቸው ጣልቃ እንድንገባ ታዘን የመከላከያ መልስ አቅርበን በቀጠሮ ላይ ይገኛል፣
- ከተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ለመልካም ስራ አፈፃፀም የተያዘው ብር ከታክስ በፊት 28,606,132.20 (ሃያ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ብር ከሃያ ሳንቲም) እንዲከፈለው በፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የፍትሐ ብሔር ፍትሕ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ስር ለተቋቋመው የግልግል ጉባኤ አቤቱታ አቅርቦ ዳይሬክቶሬቱም በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ግራ ቀኞችንን ሲያደራድር ቆይቶ ከተያዘው ገንዘብ ውስጥ ብር 19,740,645.29 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሺ ስድስት መቶ አርባ አምስት ብር ከ ሃያ ዘጠኝ ሳንቲም ) ለኢንተርፕራይዙ፤ እንዲከፈል ቀሪውን ብር 8,865,486.91 (ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስድሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም)

ኮሚሽኑ ፕሮጀክቱን ለማስጠገን ለሚያወጣቸው ወጪዎች መደጎሚያ እንዲውል በማለት ውሳኔ ሰጥቶ አፈፃፀሙ በሂደት ላይ ይገኛል፣

- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ረቂቅ ደንብ ዝግጅት  በአሁን ሰአት በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን በቀጣዩ ወር ረቂቁ ለአስተያየት ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ለመላክ በዝግጅት ላይ እንገኛለን፣
- በስድስት ወራት ውስጥ 48 የሕግ አስተያየቶችን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች እና የስራ ክፍሎች ለመስጠት ታቅዶ 46 የሕግ አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን ይህም የዕቅዱ 95.8% ነው፣
- በስድስት ወራት ውስጥ 30 የውል ሰነዶችን ማረጋገጥና ለማፅደቅ ታቅዶ ከዕቅዱ በላይ 36 የውል ሰነዶች የተረጋገጡ ሲሆን ይህም የዕቅዱ 120 % ተከናውኗል፡፡

## 1.6 የውስጥ ኦዲት

- በኮሚሽኑ የመደበኛ በጀት የገቢና የወጪ ሂሳብ አመዘጋገብ አያያዝና አጠቃቀም በደንቡና በመመሪያው መሠረት ትክክል መሆኑን በኦዲት ምርመራ ማረጋገጥ አፈጻጸም 50%፣
- በ2013 በጀት ዓመት በየወሩ የጥሬ ገንዘብ እና የተንጠልጣይ ሰነድ ቆጠራ ማካሄድ እቅድ አሥራ ሁለት ክንውን ስድስት (አፈፃፀም 50%)፣
- በፋይናንስ፣ በግዢ፣ በንብረት፣ ወዘተ ደንብና መመሪያን ላይ ለሥራ ክፍሎችና ለሠራተኞች ልዩ ልዩ የምክር አገልግሎት የመስጠት ድጋፍ ማድረግ 12 ታቅዶ ስድስት ተከናውኗል (አፈፃፀም 50%)፣
- ከመንግሥት ለፕሮጀክቶች የተፈቀደውን በጀት የወጪ ሠነዶች በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ስለመሆኑ በኦዲት ምርመራ እና ምልከታ ማድረግ አፈፃጸም 50%፣
- ድንገተኛ ኦዲት በበላይ አመራሩ ትእዛዝ መሰረት ማከናወን በሚለው በስድስት ወር ትእዛዝ አንድ ተሠርቶ ሪፖርት ተደርጓል፣

➢ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የስድስት ወራት አፈጻጸም 70.4 በመቶ ነው፡፡

## 1.7 የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ

- የሴቶች  ሁለንተናዊ  ብቃት ማጎልበትና በኢኮኖሚ መስኮች እኩል ተሳታፊነት ማረጋገጥ፣
- በሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ዙሪያ ለመረጃ ፈላጊዎች መረጃ መስጠት 6.6%፣
- ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶችን በመስኖ ሥራ ለማደራጀትና ለማጠናከር  ታቅዶ 9.6%፣
- በወጣቶች የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሴቶችን ተሳታፊነት የሚያሳይ መረጃ  ለማሰባሰብ ታቅዶ 6.92%፣

### ታቅደው ያልተከናወኑ ተግባራት

- ለሴቶችና ወጣቶች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በኮቪድ 19 ምክንያት ስልጠናው አልተሰጠም፡፡

- የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዶ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ሳይከናወን ቀርቶል፡፡
- በሁሉም የስራ ዘርፋ የሴቶች ጉዳይ ማካተትና ተቋማዊነት ማሳደግ ታቅዶ በወቅቱ በተከሰተው አለም አቀፍ ወረርሽኝ ምክንያት ሳይከናውን ቀርቷል፡፡

## 1.8 ሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት

- ከዘርፉ ስትራቴጂክ ዕቅድ የተመነዘረ ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ አፈጻጸሙን መከታተል፣ መገምገም፣
- መንግሥት ባወጣው የምዘና ስርዓት መሠረት በየወቅቱ እንዲመዘኑ ማድረግ፣ በምዘናው ውጤት መሠረትም ቀጣይ ተግባራትን ማከናወን፣
- ልዩ ልዩ የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ ዝውውር፣ የድስፐሊን፣ የቅሬታ ማስተናገጃና እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ኮሚቴዎች ማቋቋምና ተግባራዊ እንዲሆኑ መከታተል፣
- አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞች ስለ መንግሥት መመሪያዎችና ደንቦች እንዲሁም ተቋሙ ስለተቋቋመበትና ስለሚጠበቅበት ውጤት እንዲሁም ስለ መሥሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ኃላፊነት የማስተዋወቂያ ስልጠና እንዲሰጥ በማድረግ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ማድረግ፣
- የሰው ሀብት ሥራ አመራርን የተመለከቱ መመሪያዎች እንዲከለሱና አዳዲስ ጥናት እንዲጠኑ ማድረግ፣ የጥናት ውጤቶችን መገምገም፣
- ለሥራ መደቦች የሥራ ትንተና ተከናውኖ የሥራ ዝርዝር መግለጫ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣
- ደረጃውን የጠበቀ የሰው ሃብት የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ ጥናቶች እንዲጠኑ ማድረግ የተጠኑትን መገምገም፣ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣
- የሀገር ውስጥና የውጭ አገር ተሞክሮዎችን መዳሰስ፣ መቀመር፣ እንዲቀመር ማድረግ፣/ ጠቃሚ የሆኑት በሥራ እንዲተረጎሙ ማድረግ፣
- ዘመናዊ የሆነ የሰው ሀብት ሥራ አመራር እንዲኖር ለማድረግ የአሠራር ማሻሻያ ዘዴዎችን እንዲጠኑ ማድረግ፣ የተጠኑትን መገምገም፣ ማጽደቅ፣
- የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ሰርኩላሮችና አግባብነት ያላቸው መመሪያዎችን ተፈጻሚነታቸውን መከታተል፣
- ሜሪቲን የተከተለ የሰው ሀብት ምልመላና መረጣ እንዲከናወን ማድረግ፣
- ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችና አገልግሎቶች ሳይዛቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
- ደረጃውን የጠበቀ የሰው ሃብት የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ እንዲከናወን ማድረግ፣
- የሠራተኛ የግል ማህደሮች ተሟልተውና ዘመናዊ ሆነው እንዲያዙ ክትትል ማድረግ፣
- ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሰው ሃብት ሥራ አመራር ዙሪያ ለሚቀርቡ ማብራሪያዎች ህጉን መሠረት በማድረግ ማብራሪያና ምላሽ እንዲዘጋጁ ማድረግ፣

- ተጠሪ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሰው ሃይል ስምሪት ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ደንብና መመሪያ በመከተል ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ፣ አፈጻጸሙን መከታተል፤ ማረጋገጥ፤
- የሰው ኃይል እቅድ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ፣ እንዲደራጁ ተተንትነው እንዲጠናቀሩ ማድረግ፣ የመረጃዎችን ትክክለኝነት ማረጋገጥ፣ ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፣

***በስራ አመራርና ድጋፍ ፕሮግራም ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች:-***

***ያጋጠሙ ችግሮች***

- በቢሮ ጥበት ላይ ችግር መኖሩ በየጊዜው ጥያቄ ቢነሳም ለችግሩ ዕልባት መስጠት ባለመቻሉ በስራ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣
- በአንዳንድ ዳይሬክቶሬቶች የሰዉ ሀይል አለመሟላት በክፍሉ የስራ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣
- ማንኛውም የቢሮ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ግዥ በIFMIS ሶፍትዌር አማካይነት ጥያቄ ካልቀረበ ግዥ እንደማፈጽም በመደረጉ እና በስራ ክፍሎች ያሉ ሁሉም ሰራተኞች በቂ ስልጠና ባለመውሰዳቸውና በሶፍትዌሩ ጥያቄ ባለማቅረባቸው ለቢሮ መገልገያ የሚውሉ አላቂና ቋሚ ዕቃዎች ግዥ በተሟላ መልኩ መፈጸም አለመቻሉ፣
- የተሽከርካሪ እጥረት፣

***የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች***

- ለቢሮ ጥገናና ፓርቲሽንና መሰል ስራዎች 50 ሚሊዮን ብር ዝውውር ተደርጎ እንዲሰራ በማኔጅመንት ተወስኗል፡፡
- የሰዉ ሀይል እስኪሟላ ባለዉ የሰዉ ሀይል ተሸፍኖ እየተሠራ ይገኛል፡፡
- በIFMIS ሥራ ላይ የተፈጠረውን ችግር መቅረፍ እንዲቻል ስልጠና ላልወሰዱ ሠራተኞች ስልጠና እንዲሰጥ እየተጠየቀ ይገኛል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- የሰው ኃይል ዕጥረት በሚታይባቸው የሥራ ክፍሎች ብቁ የሆኑ ሠራተኞችን በመቅጠር ማሟላት፣
- ለኮሚሽኑ የተደለደሉትን ቢሮዎች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በመነጋገር ቢሮዎቹ እንዲለቀቁ ግፊት ማድረግ እና ለጥገናና ፓርቲሽን በተመደበው ገንዘብ ብቁ ተቋራጭ መርጦ በመቅጠር በጣም ባጠረ ጊዜ ችግሩ እንዲፈታ ማድረግ፣
- አዳዲስ ተጨማሪ ተሽከርካሪዎች የሚገኙበትን መንገድ ማፈላለግና ጋራዥ በብልሽት የቆሙትን ተሽከርካሪዎች በአፋጣኝ በማስጠገን ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣

# ፕሮግራም ሁለት፡ መስኖ ልማት ልማት

## ንዑስ ፕሮግራም አንድ፡ የመስኖ ጥናት፣ዲዛይንና ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም

### የንዑስ ፕሮግራሙ የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም

## ሀ. ግድብ ግንባታ

### 2.1 የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት

**መግቢያ**

የመገጭ ግድብ ፕሮጀክት የሚገኘው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ጎንደር ዞን በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ሲሆን የዚህ ግድብ ዓይነት Rock fill Dam ሆኖ የሚገነባው በተመረጠ አፈር፣ በድንጋይና በሼል (ዋልካ አፈር) ነው፡፡ ግድቡ 185 ሚሊዮን ሜ. ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም ያለው ሲሆን በሰከንድ 662 ሜ.ኩብ ትርፍ ውሃ ማስተንፈስ የሚችል ርዝመቱ 54 ሜትር የሆነ የትርፍ ውሃ ማስወገጃ አካል (spill way)፣ በሰከንድ 20 ሜ.ኩብ ውሃ መቀበልና መቆጣጠር የሚችል ቁመቱ 64.7 ሜትር የሆነ የውሃ መቀበያና መቆጣጠሪያ ማማ /Intake tower/፣ የወገቡ ስፋት 2.5 ሜትር የሆነ በሰከንድ 40 ሜ.ኩብ ዉሃ ወደ መስኖ መሬት ሊያደርስ የሚችል የመስኖ ቦይ ወይም ቱቦ እና የወገቡ ስፋት 1 ሜትር የሆነ የመጠጥ ውሃ ማስተላለፊያ ቱቦ (የሁለቱም ቱቦዎች ርዝመት 220 ሜትር ነው) የሚኖረመው ነው፡፡

የፕሮጀክቱ ግንባታ እየተከናወነ ያለው መንግስታዊ የልማት ድርጅት በሆነው በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽ የውሃ መሰረተ ልማት ሥራዎች ዘርፍ ሲሆን የጥራት ቁጥጥር እና የማማከር ሥራው ደግሞ መንግስታዊ የልማት ድርጅት በሆነው በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ኮርፖሬሽን የውሃና ኢነርጂ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ አማካይነት ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

የግንባታው ዓላማም በመገጭ ወንዝ አዋሳኝ በሆኑና በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ ከማበርከት አኳያ ከ14000 እስከ 17,000 ሄክታር የመስኖ እርሻ የማልማት ስራ እና በተጨማሪም በጎንደር ከተማ እና በጎንደር ዙሪያ በሚገኙ ትናንሽ ከተሞች ለሚኖረው ህብረተሰብ የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በመስኖው ዘርፍ የታቀዱትን የሁለተኛው አምስት አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ግቦች ለማሳካት ከተያዙት ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ2013 በጀት አመት ግብ**

በበጀት ዓመቱ 31.43% በማከናወን የግድቡን አጠቃላይ ግንባታ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 68.57% ወደ 100% ማድረስ፡፡

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

በግማሽ ዓመቱ ውስጥ የግድቡን ግንባታ 9.36 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.72 በመቶ ወይም የዕቅዱን 7.69 በመቶ በማከናወን አጠቃላይ ግንባታው በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 68.57% ወደ 69.29% ማድረስ ተችሏል፡፡

ግቦቹን ለማሳካት በ6 ወራት ውስጥ የታቀዱና የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የዋናው ግድብ የአፈርና የድንጋይ ሙሌት ስራ በክብደት 0.91% ለማከናወን ታቅዶ 0.282% ወይም የዕቅዱ 3.98% ተከናውኗል፡፡
- የዉሃ ማስተንፈሻ የሲሚንቶ ስራ በክብደት 0.33% ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም፡፡
- የውሃ ማስወጫ ማማ ግንባታ ስራ በክብደት 0.27% ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም፡፡
- የውሃ ማስወጫ ግንባታ ስራ በክብደት 1.32% ለማከናወን ታቅዶ 0.56% ወይም የዕቅዱ 42.4% ተከናውኗል፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| መገጭ | 234 | 124 | 358 | 302 | 9 | 312 | 537 | 133 | 670 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 503.996 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 154.675 ሚሊዮን ብር (30.7 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች***

***ያጋጠሙ ችግሮች፡-***

- የውሃ መቀቢያና ማስወጪያ ማማ compensation piles ስራ በሲሚንቶ እጥረት ምክንያት እና ከዚህ ቀደም በበፊቱ ንዑስ ተቋራጭ በተሰሩት የወደቁ ፓይሎች ምክንያት አሁን የሚሰሩት የማካካሻ ፓይሎች ለመስራት ማሽን በሚቆፍርበት ወቅት የማሽኑ መያዝ፡፡
- የመጀመሪያዎች ሶስት ወራት በወቅታዊዉ የዝናብ ክስተት ምክንያት ዋናዉ ተቋራጭ በዋናዉ ግድብ ላይ በዋናነት መሰራት ያለበትን የአፈር ስራ መስራት አልቻለም፡፡
- በፕሮጀክቱ ላይ ተቋራጮች አለት(ሮክ) እና ሼል ማፈንጃ በመጠቀም ባለማምረታቸዉ ምክንያት የሼልና የሮክ ምርት እንደተፈለገዉ እንዳይመረት አድርጎታል፡፡
- የጊዜያዊ ግድብ (Coffer dam) ስራ በዋናዉ ኮንትራክተር አቅም ዉስንነት መጀመር በነበረበት ወቅት አለመጀመሩ፡፡

- ዋናዉ ተቋራጭ በውሃ ማስተንፈሻ ውቅር የአርማታ ስራ በዋነኝነት በሲሚንቶ እጥረት እና በዝናብ ምክንያት ሊሰራ አልቻለም፡፡
- ጥራቱን የጠበቀ የአርማታ ቅርፅ ማስያዣ ፎርም ዎርክ በቂ አቅርቦት አለመኖር፡፡
- የግንባታ ግብአት (የሴሜንቶ ፣ የብረት አቅርቦት) እና የማሽነሪ እጥረት አፈፃፀም ላይ ትልቅ ተፅኖ ፈጥሯል፡፡
- የንዑስ-ተቋራጭ ድርጅቱ የደቃቅ አሸዋ በሚፈለገው መጠን ማቅረብ አለመቻሉ፡፡

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- ዋናው ተቋራጭ ድርጅት ከፓይል ፋውንዴሽን ስራ ጋር ተያይዞ ያሉ የውል ጉዳዮችን በፍጥነት እንዲፈታ ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገዋል በቀጣይ ሥራውን እንዲያጠናቀቅ እና የወንዝ መቀልበስ ሥራው በታቀደለት ጊዜ ውስጥ እንዲጀመር ትዕዛዝ ተሰጥቶታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ የግብአት አቅርቦት ችግሮችን እና ከንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶች ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት እንዲያሻሽል ተነግሮታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ የማካካሻ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ በደብዳቤ ተገልፆለታል፣
- በሦስት ሺፍት ሥራ እንዲጀመር የስራ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፣
- ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች በበላይ አመራሮች ተካሂደዋል እንዲሁም ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፡፡

## 2.2 የጊዳቦ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት/ተጨማሪ ግንባታዎች/

የጊዳቦ ግድብና መስኖ ልማት ኘሮጀክት ከአዲስ አበባ 390 ኪ.ሜ ላይ በኦሮሚያና በደቡብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሚገኝ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

63,000 ሚሊዮን ሜ.ኩ ውሀ የሚይዝ የዋና ግድብ፣ የውሃ መቆጣጠሪያ ማማ፣ የትርፍ ውሃ ማስወገጃ ስትራክቸር እና የውሃ ማስወጫ በመገንባት 13,400 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታሳቢ ያደረገ ሲሆን የፕሮጀክቱ ግንባታ ቀደም ሲል ተጠናቋል፡፡ በዚህ በጀት ዓመትም ተጀምረው በመካሄድ ላይ የነበሩት የተጨማሪ ካናል እና የማህበራዊ ተቋማት ግንባታ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

**የፕሮጀክቱ የ2013 በጀት ዓመት ግቦች**

- 18 ኪሎ ሜትር የግራ ዳርቻ የመስኖ ውሃ ማቅረቢያ ዋና ቦይ ግንባታን በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከነበረበት 69.8 በመቶ ወደ 100 ማድረስ እና
- የማህበራዊ ተቋማትን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከነበረበት 39.07 በመቶ ወደ 100 በመቶ በማድረስ ሁለቱንም ግንባታዎች ማጠናቀቅ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- የተጨማሪ ዋና መስኖ ውሃ ማቅረቢያ 8 ኪሎ ሜትር የግራ ዳርቻ ግንባታን 7.79 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 8.02 በመቶ በመከናወኑ አጠቃላይ ግንባታው በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ በነበረበት 69.8 በመቶ ወደ 77.82 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡
- በ6 ወራት የማህበራዊ ተቋማት ግንባታን 27.96 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 25.18 በመቶ (የዕቅዱን 90.1 በመቶ) ማከናወን በመቻሉ ግንባታውን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 39.07 በመቶ ወደ 64.25 በመቶ ማሳደግ ተችሏል፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ጊዳቦ | 18 | 4 | 22 | 462 | 57 | 519 | 480 | 61 | 541 | 1 | 1 | 1 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 230.372 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 69.636 ሚሊዮን ብር (30.2 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

**ያጋጠመ ችግር፡-** ተቋራጭ ድርጅቱ ሲሚንቶ እና ጂኦ-ሜምብሬን በሚፈለገው መጠን ማቅረብ አለመቻሉ

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- ተቋራጭ ድርጅቱ የግብአት አቅርቦት ችግሮችን እንዲፈታ ግፊት ተደርጓል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ የማካካሻ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ እና ቀሪ ስራዎችን በታቀደላቸው ጊዜ ውስጥ እንዲያጠናቅቅ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጥጠታል፣
- ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

## 2.3 አርጆ ዴዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት

**መግቢያ**

አገራችን ኢትዮጵያ ካሏት የተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ አንዱ የገፀ-ምድር የውሃ ሀብት ሲሆን ይህንን የውሃ ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ ሁኔታ ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ወንዞችን ገድቦ መያዝና የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት በተለያዩ

የአገሪቷ ተፋሰሶች የግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች በመስኖ ልማት ኮሚሽን ባለቤትነት የተጀመሩ ሲሆን ከነዚህ የግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ የአርጆ-ዴዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

የአርጆ-ዴዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በመተግበር ረገድ ያለው ቀዳሚ ዓላማ አሁን በአገሪቱ ያለውን የስኳር ፍላጎት አሟልቶ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ዋና ዋና ግቦች**

- የግድብና ተጓዳኝ ስራዎች ግንባታን በ2013 በጀት ዓመት 18.45% በማከናወን ግንባታውን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 80.67% ወደ 99.12% ማድረስ፣
  - በ2013 በጀት ዓመት የመሠረተ ልማት ቀሪ 6.14% ግንባታን በማከናወን በአመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ፣

***የስድስት ወራት አፈጻጸም፡-***

- በስድስት ወራት ውስጥ የግድብና ተጓዳኝ ስራዎች ግንባታን 5.57 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.29 በመቶ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 5.13% ነው፡፡ በዚህም አጠቃላይ የግድብ ግንባታውን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 80.67% ወደ 80.96% ማድረስ ተችሏል፡፡
- ለሠፋሪዎች የመሰረተ ልማት ግንባታን በ6 ወራት 1.36 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.16 በመቶ ተከናውኗል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የታቀዱና የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

- የዝግጅትና አጠቃላይ ስራ በክብደት 0.85% ለማከናወን ታቅዶ 0.05% ወይም የዕቅዱ 5.9% ብቻ ተከናውኗል፡፡
- የዋናውን ግድብ መከላከያ የአፈር ቁልል (embankment) ስራ 51,441 ሜ.ኩ (በክብደት 0.12%) ለማከናወን ታቅዶ 21,433.75 ሜ.ኩብ (በክብደት 0.05%) ወይም የዕቅዱ 41.66% ተከናውኗል፡፡
- በግድቡ አናት ላይ የመንገድ መሰረተ ልማት ለመገንባት በክብደት 0.16% ለማከናወን ታቅዶ 0.09% ወይም የዕቅዱ 56.3% ተከናውኗል፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| አርጆ | 340 | 79 | 419 | 210 | 1 | 211 | 550 | 80 | 630 | 3 | 1 | 4 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 214.293 ሚሊዮን ብር ቢታቀድም ተቋራጩ ክፍያ ባለመጠየቁ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ የዋለ ገንዘብ የለም፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮች***

- የኮርቻ ግድብ (Saddle Dam) ዲዛይን ለውጥ መዘግየት፣
- የኮርቻ ግድብ የሚገነባው ተቋራጭ ድርጅት በሚፈለገው ደረጃ የግንባታ ማሽነሪ በወቅቱ ማቅረብ አለመቻሉ፣
- የትርፍ ውሃ ማስወጫያ ውቅር ግንባታ ለማስጀመር የሲምነቶ እጥረት፣
- የተራዘመ የዝናብ ወቅት ማጋጠሙ፣

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- አማካሪ ድርጅቱ የኮርቻ ግድብ (Saddle Dam) ዲዛይን በፍጥነት እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል፣
- የትርፍ ውሃ ውቅር (Spillway) ግንባታ የሚያካሂደው ተቋራጭ ድርጅት አፈፃጸሙን ማሻሻል የሚያስችለውን ዕቅድ እንዲያስገባ ተደርጓል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

## 2.4 የዛሬማ ሜይ ዴይ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት

***መግቢያ***

ይህ ፕሮጀክት የሚገኘው በትግራይ ብሄራዊ ክልል በምእራብ ዞን በወልቃይት ወረዳ ሆኖ ወልቃይት ላይ እየተገነባ ለሚገኘው የስኳር ልማት ፕሮጀክት በ40 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳን በመስኖ ለማልማት የታቀደ ነው፡፡ ግድቡ 805 ሜትር ርዝመት፣152 ሜትር ከፍታ እንዲሁም 3 ቢሊዮን 497 ሚሊዮን ሜ. ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም ያለው ሲሆን የግድቡ ግንባታ በስኳር ኮርፖሬሽን ባለቤትነት በ2004 ዓ.ም ተጀምሮ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተላልፎ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ እስካሁን የፕሮጀክቱ ፊዚካል አጠቃለይ አፈጻጸም 91.80 ሲደርስ የፋይናንስ አፈጻጸሙም 89 በመቶ ደርሷል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የዛሬማ ሜይዴይ ግድብ ግንባታ ዓላማ 40 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳን በመስኖ ማልማት የሚያስችል በቂ ውሃ እንዲቋጥር በማድረግ ወልቃይት ላይ እየተገነባ ለሚገኘው የስኳር ልማት ፕሮጀክት አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የበጀት ዓመቱ ግቦች፡-**

- በበጀት ዓመቱ የግድቡን ግንባታ 6.83 በመቶ በማከናወን አጠቃላይ ግንባታውን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከነበረበት 92.51% ወደ 99.34% ማድረስ፡፡

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

በስድስት ወራት በጥቅል 2.98 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.16 በመቶ ወይም የዕቅዱን 5.37% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የግድቡን የግንባታ አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 92.51 ወደ 92.67% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ውጤቱን ለማሳካት የተከናወኑትን ዝርዝር ተግባራት በተመለከተ፡-**

- **የውሃ ማስወጫ ዋሻ** (Irrigation Intake Pressure Tunnel) **ሥራ፡-**
  - 4688.92 ሜትር ኪዩብ የኮንክሪት ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 2095 ሜትር ኪዩብ የኮንክሪት ሥራ (44.67%) ተከናውኗል፡፡
  - 8866.8 ካሬ ሜትር የስርገት መከላከያ ፒቪሲ ንጣፍ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 5377.61 ካሬ ሜትር (60.64%) ተከናውኗል፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ዛሬማ ሜይዴይ | 149 | 14 | 163 | 38 | 4 | 42 | 187 | 18 | 205 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 388.7 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 25.49 ሚሊዮን ብር (6.6 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

**ያጋጠሙ ችግሮች፡-**

- ዋናው ተቋራጭ ድርጅት ለንዑስ-ተቋራጭ ድርጅቱ በወቅቱ ክፍያ አለመፈፀሙ፣
- የንዑስ-ተቋራጭ ድርጅቱ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን፣
- ከኮቪድ-19 ጋር ተያይዞ ንዑስ-ተቋራጭ ድርጅቱ የሚፈለገውን የሰው ኃይል አለማግኘት፣
- በክልሉ በተጀመረው የህግ ማስከበር እንቅስቃሴ ምክንያት የግንባታ ሥራ መቆሙ፣

**የመፍትሄ እርምጃዎች፡-**

- ዋናው ተቋራጭ ድርጅት ለንዑስ-ተቋራጭ ድርጅቱ ክፍያዎችን በወቅቱ እንዲከፍል ምክክር ተደርጓል፣
- የንዑስ-ተቋራጭ ድርጅቱ አፈፃፀም እንዲያሻሽል ደብዳቤ ተፅፏል፣
- በክልሉ ከሚካሄደው የህግ ማስከበር እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ በጊዚያዊነት ፕሮጀክቱ እንዲቆም ትዕዛዝ ተሰጥቷል፣

# ለ. የመስኖ መሬት ዝግጅት

## 2.5 የኢትዮጵያ ናይል መስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክት

**መግቢያ**

ይህ ፕሮጀክት የሚገኘው በአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ጎንደር ዞኖች በደምቢያ፣ በሊቦ ከምከምና ፎገራ ወረዳዎች ነው፡፡ በፕሮጀክቱ አማካይነት የሚዘጋጀውን የመስኖ መሬት በተመለከተ በርብ 3000 ሄ/ር እና በመገጭ ሰራባ 4000 ሄ/ር በድምሩ 7000 ሄክታር የመስኖ መሬት ሲሆን የመገጭ ሰራባ ግንባታው ተጠናቆ ሲመረቅ የርብ መስኖ አውታር ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የመገጭ ሰራባ መስኖ አውታር ግንባታ ከጣና ኃይቅ ውኃ በኤሌክትሪክ ፓምፕ በመሳብ 4,000 ሄ/ር እና የርብ መስኖ ፕሮጀክት ከርብ ግድብ ከሚገኘዉ ዉሃ 13,000 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ የመገጭ ሰራባና ርብ መስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክቶች የመስኖና ድሬኔጅ ልማት፣ የግብርናና ገበያ ልማት እና የግንባታ ቁጥጥርና የመስኖ መሰረተ ልማት የማስተዳደር /operation & maintenance/ ኮምፐነንቶችን አካተው ይዘዋል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

ፕሮጀክቶቹ በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች ማለትም በመገጭ ሰራባና ርብ መስኖ አውታር ግንባታዎች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው ህብረተሰብ የምግብ ዋስትናቸውን በማረጋገጥ የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል ነው፡፡

**የ2012 በጀት ዓመት የፕሮጀክቱ ግብ**

- የርብ መስኖና ድሬኔጅ ግንባታን በበጀት ዓመቱ 20.9 በመቶ በማከናወን አጠቃላይ ግንባታው በ2012 በጀት አመት መጨረሻ ከነበረበት 79 በመቶ በማከናወን ፕሮጀክቱን 100% ማጠናቀቅ፡፡

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

በግማሽ ዓመቱ የርብ መስኖ አውታር ግንባታን 2.6 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም፡፡ አጠቃላይ የመስኖ አውታር ግንባታው አፈጻጸምም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ በነበረበት 79% ላይ ይገኛል፡፡

- *ታቅዶ ያልተከናወነ ሥራ፡-* የውሃ ማጠንፈፊያና ማፋሰሻ ቦይ ግንባታ ስራን ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም፡፡

**የበጀት አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 50.0 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 12.14 ሚሊዮን ብር (24.3 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠመ ችግር፡-*** የተቋራጭ ድርጅቱን ውለታ በታቀደለት ጊዘ ውስጥ አለመጠናቀቁ እና አዲስ ተቋራጭ ድርጅት የመቅጠር ሂደት ረጅም ጊዜ መውሰድ፣

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-** የተቋራጭ ድርጅቱ ውስታን የማቋረጥ ሂደት በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ጥረት በመደረግ ላይ ሲሆን በተጨማሪም ተቋራጭ ድርጅት ቅጥር ለመፈፀም ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## 2.6 የወልመል የመስኖ ልማት ፕሮጀክት

***መግቢያ***

የመስኖ ልማት ኮሚሽን በ 2012 የበጀት አመት ግንባታቸውን ለማስጀመር በእቅድ ከያዛቸው ፕሮክቶች አንዱ የወልመል የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ሲሆን ፕሮጀክቱም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስ በባሌ ዞን ደሎመና ወረዳ ውስጥ የሚተገበር ይሆናል፡፡ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ 3 ሜትር ከፍታ እና 50 ሜትር ርዝመት ያለው የወንዝ መቀልበሻ እና 30 ኪ.ሜ. ርዝመት ያለው መጋቢ የወሃ ቦይ ግንባታ የሚካሄድ ሲሆን 11,040 ሄክታር ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ግንባታም የሚከናወን ይሆናል፡፡ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሁለት አገር በቀል ተቋራጭ ድጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን አንደኛው ተቋራጭ ድርጅት የወንዝ መቀልበሻ እና መጋቢ የወሃ ቦይ ግንባታ ሥራውን ሲያከናውን ሁለተኛው ተቋራጭ ድርጅት ደግሞ የመስኖ አውታር ግንባ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የወልመል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በመተግበር ረገድ ያለው ቀዳሚ ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡** -

- የወንዝ መቀልበሻ እና ዋና ቦይ ስራዎች ግንባታን 45.88% ማከናወን፣
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን 55.8% ማከናወን፣

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- የወልመል የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን (Lot-1) በበጀት ዓመት አጋማሽ 22.22 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 11.52% (ወይም የዕቅዱን 51.85 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ የወንዝ መቀልበሻ የግንባታ አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 18 በመቶ ወደ 29.52 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡
- የወልመል የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን (Lot-2) በ6 ወራት ውስጥ 30.65 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 4.17 በመቶ (ወይም የዕቅዱን 13.6 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ የግንባታውን አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 9.75 በመቶ ወደ 13.92 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የታቀዱና የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

**ሎት 1**

- አጠቃላይ ስራዎችን 1.8% ለማከናወን ታቅዶ 1.35% ወይም የዕቅዱ 75%፣
- ዳይቨርሽን ዊርና የዋና ቦይ አናት መቆጣጠሪያ ስራን 1.45% ለማከናወን ታቅዶ ሳይከናወን ቀርቷል።
- የፊደር ካናል ስራን 13.5% ለማከናወን ታቅዶ 8.2% ወይም የዕቅዱ 60.7% ተከናውኗል።

**ሎት 2**

- የመጀመሪያ ካናል ግንባታ ስራን 6.3% ለማከናወን ታቅዶ 1.2% ወይም የዕቅዱ 19.8%፣
- የቢሮና የመኖሪያ ቤት ስራ አብዛኛው ሲጠናቀቅ
- የመንገድ ግንባታ ስራን 5.6% ለማከናወን ታቅዶ 1.3 ወይም የዕቅዱ 23.2% ተከናውኗል።

**በግማሽ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ወልመል | 1048 | 225 | 1273 | 141 | 12 | 152 | 1189 | 236 | 1425 | 2 | 2 | 4 |

**የበጀት አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 564.29 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 151.58 ሚሊዮን ብር (26.9 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል።

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ**

**ያጋጠሙ ችግሮች**

**ሎት አንድ፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ ሲሚንቶ እና ፌንጂ በሚፈለገው መጠን ማቅረብ አለመቻሉ፣
- የወንዝ መቀልበሻ መሰረት ቁፋሮ እና ፍተሻ ሥራ በወቅቱ አለመጠናቀቅ፣
- አጋጥሞ ከነበረው የሥራ መጠን ለውጥ ጋር ተያይዞ ተቋራጭ ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ አለመግባቱ፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯ

**ሎት 2፡-** ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ ማሽኖችን እና ግብአት አለማቅረብ

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-**

**ሎት አንድ፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ ሲሚንቶ እና ፈንጂ በሚፈለገው መጠን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል፣
- የወንዝ መቀልበሻ መሰረት ቁፋሮ እና ፍተሻ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ደብዳቤ ተፅፎለታል፣
- ከሥራ መጠን ለውጥ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፣

- ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች ተካሂዷል እንዲሁም ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

**ሎት 2፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት እንዲያቀርብ ደብዳቤ እና ማስጠንቀቂያ ተፅፎለታል፣
- ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች ተካሂዷል እንዲሁም ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

## 2.7 የጨልጨል የመስኖ ልማት ፕሮጀክት

**መግቢያ**

የጨልጨል የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በ2012 በጀት ዓመት የተያዘ አዲስ ፕሮጀክት ሲሆን የሚገኘውም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባሌ ዞን ራይቱ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ ቁመቱ 46.5 ሜትር የሆነ ግድብ የሚገነባ ሲሆን 4,146 ሄክታር ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ግንባታም የሚከናወን ይሆናል፡፡ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሁለት አገር በቀል ተቋራጭ ድርጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን አንደኛው ተቋራጭ ድርጅት የግድብ ግንባታ ሥራውን ሲያከናውን ሁለተኛው ተቋራጭ ድርጅት ደግሞ የመስኖ አውታር ግንባታ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የጨልጨል ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡ -**

- የወንዝ መቀልበሻ እና ዋና ቦይ ስራዎች ግንባታን 53.17% ማከናወን፣
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን 57% ማከናወን፣

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- የጨልጨል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (Lot-1) በበጀት ዓመት አጋማሽ 23.24% ለማከናወን ታቅዶ 4.83% (ወይም የዕቅዱን 20.79 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ የግድቡን የግንባታ አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 5.89 በመቶ ወደ 10.72 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

- **የጨልጨል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (Lot-2) በበጀት ዓመት አጋማሽ 28.58% ለማከናወን ታቅዶ 4.81% (ወይም የዕቅዱን 16.83 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ የግንባታውን አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 10.22 በመቶ ወደ 15.03 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡**

**በግማሽ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ጨልጨል | 289 | 18 | 307 | 119 | 0 | 119 | 407 | 18 | 425 | 2 | 1 | 3 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 491.815 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 44.72 ሚሊዮን ብር (9.1 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች***

***ያጋጠሙ ችግሮች***

**ሎት 1**

- ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት አለማቅረብ፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ ቀድሞ መስራት የሚገባውን ሥራዎች አለማከናወኑ፣
- የግድብ የመሰረተ ቁፋሮ እና ፍተሻ በወቅቱ አለመጠናቀቅ፣
- ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ከሚደረግብት አከባቢ ጋር ተያይዞ ያሉ የጂኦሎጂ/ጂኦቴክኒክ ምርመራዎችን በድጋሜ ማድረግ ማስፈለጉ፣

**ሎት 2፡-** ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት አለማቅረብ

***የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-***

**ሎት 1**

- *ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት እንዲያቀርብ ትዕዛዝ እና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተፅፎበታል፣*
- *ተቋራጭ ድርጅቱ ቀድሞ መስራት የሚገባውን ሥራዎች ከወዲሁ እንዲያከናውን ተነግሮታል፣*
- *የግድብ የመሰረተ ቁፋሮ እና ፍተሻ በወቅቱ እንዲጨርስ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል፣*
- *ያለውን የጂኦሎጂ/የጂኦቴክኒክ ችግር ለመፍታት የቴክኒክ ቡድን ተቋቅሞ ሙያዊ አስተያየቶችን እንዲያቀርብ ተደርጓል፣*
- *ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች ተካሂዷል እንዲሁም ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣*

- *በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣*

**ሎት 2፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት እንዲያቀርብ ትዕዛዝ እና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተፅፎበታል፣
- ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች ተካሂዷል እንዲሁም ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

## 2.8 የላይኛው ጉደር የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት

**መግቢያ**

የላይኛው ጉደር የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በ2012 በጀት ዓመት የተጀመረ ፕሮጀክት ሲሆን የሚገኘውም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ሸዋ ዞን ጉደር ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ በፕሮጀክቱ 40.6 ሜትር ከፍታ ያለው ግድብ ግንባታ የሚካሄድ ሲሆን 4,926 ሄክታር ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ግንባታም የሚከናወን ይሆናል፡፡ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሁለት አገር በቀል ተቋራጭ ድርጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን አንደኛው ተቋራጭ ድርጅት የግድብ እና ተያያዥ ሥራዎች ግንባታ የሚያካሂድ ሲሆን ሁለተኛው ተቋራጭ ድርጅት ደግሞ የመስኖ አውታር ግንባታ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

የላይኛው ጉደር ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክትን ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡-**

- የወንዝ መቀልበሻ እና ዋና ቦይ ስራዎች ግንባታን 34.28% ማከናወን፣
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን 71.63% ማከናወን፣

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- የላይኛው ጉደር የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (Lot-1) በበጀት ዓመት አጋማሽ 13.38% ለማከናወን ታቅዶ 3.61% (ወይም የዕቅዱን 26.98 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ የግድቡን የግንባታ አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 16.0 በመቶ ወደ 19.61 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡
- የጨልጨል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (Lot-2) በበጀት ዓመት አጋማሽ 8.13% ለማከናወን ታቅዶ 1.21% (ወይም የዕቅዱን 14.88 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ የግንባታውን አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 5.05 በመቶ ወደ 6.26 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**በግማሽ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የላይኛው ጉደር | 294 | 53 | 347 | 37 | 3 | 40 | 331 | 56 | 386 | 2 | 1 | 3 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 378.764 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 79.2 ሚሊዮን ብር (20.9 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ***

***ያጋጠሙ ችግሮች፡-*** የክረምቱ ወቅት የተራዘመ መሆኑ እና የተሸከርካሪ እጥረት መከሰት፣

**ሎት 1፡-**

- የተራዘመ የዝናብ ወቅት ማጋጠሙ፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በዝግጅት ሥራዎች ላይ ብቻ ማተኮሩ፣
- የዲዛይን ማሻሻያ ሥራዎች በወቅቱ ተጠናቆ ለተቋራጭ ድርጅቱ አለመሰጠት፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት አለማቅረብ፣

**ሎት 2፡-**

- የተራዘመ የዝናብ ወቅት ማጋጠሙ፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በጨረታ ሂደት ላይ ብቻ ማተኮሩ፣
- የዲዛይን ማሻሻያ ሥራዎች በወቅቱ ተጠናቆ ለተቋራጭ ድርጅቱ አለመሰጠት፣
- ከመሬት አቅርቦት ጋር ተያይዞ ያሉ ጉዳዮች በወቅቱ አለመፈታት፣

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-**

**ሎት 1**

- ተቋራጭ ድርጅቱ የማካካሻ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ደብዳቤ ተፅፎለታል፣
- አማካሪ ድርጅቱ የዲዛይን ማሻሻያዎችን በፍጥነት አጠናቆ ለተቋራጭ ድርጅቱ እንዲሰጥ ግፊት ተደርጓል፣
- ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች ተካሂዷል እንዲሁም ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

**ሎት 2 ፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ የማካካሻ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ደብዳቤ ተፅፎለታል፣

- አማካሪ ድርጅቱ የዲዛይን ማሻሻያዎችን በፍጥነት አጠናቆ ለተቋራጭ ድርጅቱ እንዲሰጥ ግፊት ተደርጓል፣
- ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች ተካሂዷል እንዲሁም ተደጋጋሚ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

## 2.9 የላይኛው ርብ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት

***መግቢያ***

የላይኛው ርብ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በ2012 በጀት ዓመት የተያዘ አዲስ ፕሮጀክት ሲሆን የሚገኘውም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ጎንደር ዞን ሊቦከምከም እና ፎገራ ወረዳዎች ውስጥ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ የወንዝ መቀልበሻ ግንባታ የሚካሄድ ሲሆን 6,002 ሄክታር ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ግንባታም የሚከናወን ይሆናል፡፡ በፕሮጀክቱ ግንባታ አንድ አገር በቀል ተቋራጭ ድርጅት የሚሳተፍ ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የላይኛው ርብ የወንዝ መቀልበሻና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡-** የወንዝ መቀልበሻ እና ዋና ቦይ ስራዎች ግንባታን እና የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን በ2013 በጀት ዓመት 39.2% ማከናወን፣

**የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም**

በ6 ወራት ውስጥ የላይኛው ርብ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን 14.13 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 3.83% ወይም የዕቅዱን 27.11% ነው፡፡ በዚህም አጠቃላይ የግንባታውን አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 4.65 በመቶ ወደ 8.48 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የታቀዱና የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

- የካምፕ ግንባታ ስራን 3.2% ለማከናወን ታቅዶ 3.0% ወይም የዕቅዱን 93.8% ማከናወን ተችሏል፡፡

**በግማሽ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የላይኛው ርብ | 391 | 61 | 452 | 96 | 16 | 111 | 486 | 77 | 563 | 2 | 1 | 3 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 237.156 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 30.878 ሚሊዮን ብር (13 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል።

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ***

***ያጋጠሙ ችግሮች፡-***

- የተራዘመ የዝናብ ወቅት ማጋጠሙ፣
- ለጥገና ሥራ ተብሎ ከርብ ግድብ ከሚለቀቀው ውሃ ጋር ተያይዞ ተቋራጭ ድርጅቱ የወንዝ ማስቀልበሻ ውቅር ግንባታ ሥራ በወቅቱ መጀመር አለመቻሉ፣
- የካሳ ግምት ሥራ ረጅም ጊዜ በመውሰዱ ለተቋራጭ ድርጅቱ ቦታ ማስለቀቅ አለመቻሉ፣

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ የማካካሻ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ደብዳቤ ተፅፎለታል፣
- የወንዝ ማስቀልበሻ ውቅር ግንባታ በወቅቱ እንዲጀመር ግፊት ተደርጓል፣
- የካሳ ግምት ሥራዎች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ጥረት ተደርጓል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

## 2.10 ዱብቲ ዳይክና የመስኖ አውታር ጥገና

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

የዱብቲ ዳይክና የመስኖ ጥገና ፕሮጀክት የሚካሄደው በአፋር ክልል ዱብቲ ወረዳ ውስጥ ሲሆን እንዲያለማ የሚጠበቀው የመስኖ መሬት ስፋት 2500 ሄክታር ነው። የዚህ ፕሮጀክት ትግበራ ዐቢይ ዓላማ የተበላሹና ጥገና የሚስፈልጋቸውን ካናሎችና ሌሎች የውሃ ውቅሮችን አስፈላጊ የሆኑ የጥገና ሥራዎች ግንባታ በማከናወን የመስኖ መሬቱን ቀድሞ ወደነበረበት በመመለስና ወደ ሙሉ ልማት በማስገባት የአካባቢውን ህብረተስብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ ማድረግ ነው።

የመስኖ አውታሩን በመጠገን ዘላቂ የሆነ የልማት አገልግሎት እንዲሠጥ በማድረግ የአካባቢውን ነዋሪ ተጠቃሚ ማድረግ።

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-**

- የዱብቲ ዳይክ ጥገናና የመስኖ አውታር ግንባታን በ2013 በጀት ዓመት 57% ተግባራትን በማከናወን በአመቱ መጨረሻ 67% ማድረስ ነው፣

**የ6 ወራት አጻጸም፡-** የዳይክና የመስኖ ጥገና ሥራዎችን 17 በመቶ ለማከናወን ቢታቀድም አልተከናወነም።

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 70.96 ሚሊዮን ብር ቢታቀድም ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ የዋለ ገንዘብ የለም።

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች***

***ያጋጠሙ ችግሮች፡-***

- የአማካሪ ድርጅት ቅጥር በወቅቱ አለመፈፀሙ፣
- በአከባቢው አጋጥሞ በነበረው የጎርፍ ችግር ምክንያት ተቋራጭ ድርጅቱ ቶሎ ወደ ሥራ መግባት አለመቻሉ፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት አለማቅረብ፣

***የመፍትሄ እርምጃዎች***

## 2.11 የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት

***የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-***

የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የሚገኘው በትግራይ ክልል ውስጥ ሲሆን እንዲያለማ የሚጠበቀው የመስኖ መሬት ስፋት 10000 ሄክታር ነው። የዚህ ፕሮጀክት ትግበራ ዐቢይ ዓላማ የአካባቢውንና የክልሉን ብሎም የአገሪቱን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ነው።

***የበጀት ዓመቱ ግብ፡-*** የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራን አስጀምሮ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 29% ማከናወን ነው።

***የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም***

በግማሽ ዓመቱ ውስጥ የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት 1) 10 በመቶ እና ሎት 2 13 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም።

***የፋይናንስ አጠቃቀም፡-*** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 360.0 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 29.99 ሚሊዮን ብር (8.3 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል።

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች***

***ያጋጠመ ችግር፡-*** በክልሉ ከተጀመረው የህግ ማስከበር ጋር ተያይዞ የአማካሪ ድርጅት ቅጥር በወቅቱ አለመፈፀሙ፣

## 2.12 አጂማ ጫጫ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት

***የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-***

የአጂማ ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የሚገኘው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን በአንጎሎላ ጠራ ወረዳ ውስጥ ሲሆን እንዲያለማ የሚጠበቀው የመስኖ መሬት ስፋት 7000 ሄክታር ነው። የዚህ ፕሮጀክት ትግበራ ዐቢይ ዓላማ የአካባቢውን፣ የክልሉን ብሎም የአገሪቱን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ነው።

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የአጂማ ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራን አስጀምሮ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 21 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም**

- በግማሽ ዓመቱ ውስጥ የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት 1) 1 በመቶ እና ሎት 1 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም፡፡
- የአጂማ ጫጫ የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (Lot-3) በበጀት ዓመት አጋማሽ 4.0 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 4.57 በመቶ (ወይም ከዕቅድ በላይ 114.25 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ የግድቡን ግንባታ እስከ 2013 በጀት ዓመት 6 ወራት መጨረሻ ወደ 4.57 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

**ያጋጠሙ ችግሮች፡-**

**ሎት አንድ**

- የተቋራጭ ድርጅት ቅጥር ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣
- ከካሳ ግምት ሥራ ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ፍጥነት የግንባታ ቦታዎችን በወቅቱ ማስለቀቅ አለመቻሉ፣

**ሎት ሁለት**

- **የተቋራጭ ድርጅት ቅጥር አለመፈፀሙ፣**

**ሎት ሶስት**

- **ከካሳ ግምት ሥራ ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ፍጥነት የግንባታ ቦታዎችን በወቅቱ ማስለቀቅ አለመቻሉ፣**

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- የካሳ ግምት ሥራዎች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ጥረት ተደርጓል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 632.1 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 636.51 ሚሊዮን ብር (100.7 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

## 2.13 ካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የሚገኘው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ውስጥ ሲሆን እንዲያለማ የሚጠበቀው የመስኖ መሬት ስፋት 1800 ሄክታር ነው፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ትግበራ

ዐቢይ ዓላማ የአካባቢውን፣ የክልሉን ብሎም የአገሪቱን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራን አስጀምሮ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 35 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም**

- የካሊድ **ዲጆ** መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በበጀት ዓመት አጋማሽ 6.0 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 1.15 በመቶ (ወይም የዕቅዱን 19.17 በመቶ) በማከናወን አጠቃላይ ግንባታውን እስከ 2013 በጀት ዓመት 6 ወራት መጨረሻ ወደ 1.15 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 42.857 ሚሊዮን ብር ቢታቀድም ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ የዋለ ገንዘብ የለም፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች***

***ያጋጠመ ችግር፡-*** ከካሳ ግምት ሥራ ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ፍጥነት የግንባታ ቦታዎችን በወቅቱ ማስለቀቅ አለመቻሉ፣

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- የካሳ ግምት ሥራዎች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ጥረት ተደርጓል፣
- በኮሚሽኑ በኩል የክትትል ሥራውን ለማጠናከር ተሞክሯል፣

## 2.14 የሌሎች አዳዲስ ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ደረጃ

*በ2013 በጀት ዓመት ሊጀመሩ የታቀዱ የገላና፣ ግልገል አባይ፣ ዳቡስና መገጭ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች እንዲሁም ቦረና፣ ሀላይደጌና ሸንሌ የከርሰ ምድር ውሃ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች* የዲዛይንና የጨረታ ሂደታቸውን ጨርሰው ለግንባታ ዝግጁ ባለመሆናቸው በዚህ ግማሽ ዓመት ውስጥ የተከናወነ የግንባታ ስራ የለም፡፡ ሆኖም በግማሽ ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑትን ሥራዎች በተመለከተ

- ለገላና፤ ለግልገል አባይ፤ ለዳቡስና ለመገጭ የዲዛይን ክለሳ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፤
- ለአንገር፤ ለኬጦና ወይቦ በመጀመሪው ግማሽ ዓመት ውስጥ ጨረታ ወጥቷል፤
- ሃላይደጌ ፕላንና ልማት ኮሚሽን በግምገማ ላይ ይገኛሉ፤
- ሸንሌ በኢ/ኮ/ዲ/ሱ/ስ/ኮ 4,000 ሄር በዲዛይን ስራ ላይ ይገኛል፡፡
- ቦረና መረጃ ባለመገኘቱ ምንም ስራ አልተጀመረም፤
- ሁሉም የጨረታ ሂደት ማለፍ የሚኖርባቸው ሲሆን ከውለታ በኋላ የሥራ ማስጀመሪያ ጊዜ አስፈላጊ ይሆናል

## 2.12 የተማሩ ወጣቶች መስኖ ልማት ፕሮግራም

**መግቢያ**

በአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የተማሩ ምሩቃን ወጣቶች የሥራ አጥነት ሁኔታ እያደገ ይገኛል፡፡ ይህን የተከሰተ ችግር ለመቅረፍ መንግስት የሚቻለውን ሁሉ ጥረት በማድረግ ላይ ቢሆንም የችግሩ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት የኮሚሽኑ መ/ቤትም የበኩሉን ለመወጣት እንዲያስችለው እነዚህኑ የተማሩ ወጣቶች በኮሜርሻል መስኖ ልማት በማሰማራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ዕቅድ ይዞ እንቅስቃሴ በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለተደራጁ ምሩቃን ወጣቶች የመስኖ መሬት እና ቴክኖሎጂ በማቅረብ በተቀናጀ የመስኖ ልማት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊ በማድረግ፣ ምልመላና ስልጠና በመስጠት፣ ግብዓት በማቅረብና ገበያ ተኮር የመስኖ ሥራ በመስራት ቀደም ሲል የመስኖ አውታር ከተዘረጋላቸው የመስኖ መሬቶችና ወደፊት ከሚገነቡ ውሃ ገብ የመስኖ መሬቶች ውስጥ የተወሰነውን ለወጣቶች በመስጠት ወደ ልማት ማስገባት እንዲቻል በ2013 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 800,000,000 በጀት እንዲያዝ ተደርጓል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች**

በወጣቶች መስኖ ልማት ፕሮግራም ረገድ የበጀት ዓመቱ ግቦች

- በ8 ክልሎች (አፋር፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ብ/ብ/ህ፣ አማራ፣ ትግራይ፣ ሲዳማ፣ ሶማሌ፣ ኦሮሚያ) 28,500 ሄ/ር የእርሻ መሬት የመለየት ስራ ማከናወን፣
- በ33,000 ሄ/ር በተለዩ መሬቶች ላይ የመሰረተ ልማት ማሟላት፣
- 8,800 የተማሩ ወጣቶችን መልምሎ እና አደራጅቶ ወደ ስራ ማስገባት፣
- መለስተኛ ሙያ ላላቸው 73,700 ወጣቶች ተጨማሪ የስራ እድል መፍጠር፣

**የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

**ሀ. ለወጣቶች የሚውል የእርሻ መሬት መለየት**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | የሚገኝበት ክልል | የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ6 ወሩ እቅድ ክንውን | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | በ% | |
| 1.1 | ጊዳቦ | ኦሮሚያ | 3,500 | 3,500 | 3000 | 85.7 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |
| 1.2 | ተንዳሆ/ዱብቲ | አፋር | 6,000 | 6,000 | 6000 | 100 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |
| 1.2 | ጣና በለስ | አማራ | 4,000 | 3,000 | 3000 | 100 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |
| 1.3 | አርጆ ዴዴሳ | ኦሮሚያ | 10,000 | 4,000 | 0 | 0 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.4 | ጊዳቦ | ሲዳማ | 3,000 | 3,000 | 700 | 23.3 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |
| 1.5 | ኩለን | ሶማሊ | 1,000 | 1,000 | 2000 | 200 | በተጨማሪ 1000 ሄ/ር ክልሉ በመለየቱ |
| 1.6 | ፋፈን | | 1,000 | 1,000 | 1000 | 100 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |
| 1.7 | ሀረዋ | | 1,000 | 1,000 | 1000 | 100 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |
| 1.8 | ጎዴ ሳይት | | 2,000 | 2,000 | 2000 | 100 | ቀድሞ በውሳኔ የተለየ |
| | **ድምር** | | **25,500** | **22,500** | **17,700** | **78.7** | የኦሞ ኩራዝ፣ ራያ ቫሊ እና ኤልዌሮ ሳይገባ |

**ለ. በተለዩ መሬቶች ላይ መሰረተ ልማት ማሟላት**

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 | ጊዳቦ | ኦሮሚያ | 3500 | 1500 | 1400 | 93.3 | ተቋራጭ የኦሮሚያ ው/ስ/ኮ/ኮርፖሬሽን |
| 2.2 | ጣና በለስ | አማራ | 4,000 | 2000 | 1000 | 50 | ተቋራጭ የአማራ ው/ሥ/ኮ ድርጅት ነው |
| 2.3 | ተንዳሆ ሳይት | አፋር | 6,000 | 6,000 | 4629.5 | 77.2 | ተጨማሪ የቦይ ጥገና ለኢኮስኮ ውለታ ተገብቷል |
| 2.4 | አርጆ ዴዴሳ | ኦሮሚያ | 10,000 | 4,000 | 0 | 0 | የወሰን ማስከበ ችግር ያለበት በመሆኑ |
| 2.5 | ጊዳቦ | ሲዳማ | 3,000 | 3,000 | 0 | 0 | በቅርቡ ልየታ የተካሄደ በመሆኑ |
| 2.6 | ፋፈን | ሶማሌ | 1,000 | 1,000 | 0 | 0 | ፋፈን እና የኩለን ክልሉ ቅድሚያ ሰቶ በቅርቡ የለያቸው ናቸው |
| 2.7 | ኩለን | | 1,000 | 1,000 | 0 | 0 | |
| 2.8 | ሀረዋ | | 1,000 | 1,000 | 0 | 0 | |
| 2.9 | ጎዴ ሳይት | | 2,000 | 2,000 | 2684 | 134 | በተጨማሪም የፌደራል ዲዛይን ኮ/ን የመጀመሪያ ደራፊት ዲዛይን አቅርቦ በመታየት ላይ ይገኛል |
| | **ድምር** | | **25,500** | **21,500** | **11,714** | **54.5** | |

**ሐ. ወጣቶችን መመልመል፣ ማሰልጠንና የማደራጀት ሥራ ማከናወን**

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1 | አርጆ ዴዴሳ | ኦሮሚያ | 2,400 | 1,200 | 0 | 0 | የመሬት ዝግጅት ባለማለቁ አልተከናወነም |
| 4.3 | ጣና በለስ | አማራ | 160 | 160 | 0 | 0 | ›› ›› |
| 4.5 | ተንዳሆ ሳይት | አፋር | 1230 | 0 | 0 | 0 | ›› ›› |
| 4.6 | ጊዳቦ | ኦሮሚያ | 345 | 345 | 0 | 0 | ›› ›› |
| 4.7 | ጊዳቦ | ሲዳማ | 720 | 0 | 0 | 0 | ›› ›› |
| 4.8 | 4ቱም ሳይቶች | ሶማሊ | 383 | 383 | 0 | 0 | ›› ›› |
| | **ድምር** | | **5,238** | **2,088** | 0 | **0** | የኦሞ ኩራዝ፣ ራያ ቫሊ እና ኤልዌሮ ሳይገባ |

**መ. ለወጣቶች መለስተኛ የካምፕ ግንባታ እና መሰረታዊ ፍላጎት በማሟላት ስራ መስጀመር**

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1 | አተንዳሆ | አፋር | 100 | 20% | 0% | 0 | የነባር ካምፕ ጉዳይ ከስኳር ኮ/ን የተጀመረው ንግግር ባለማለቁ |
| 4.2 | ጊዳቦ | ኦሮሚያ | 100 | 70% | 30% | 42.9 | ለኮሮሚያ ኮ/ስራዎች ኮ/ን ውላታ ተገብቷል |
| 4.3 | ጣና በለስ | አማራ | 100 | 70% | 30% | 42.9 | ለአማራ ውሃ ስ/ኮርሬሽን ውለታ ተገብቷል |
| | **ድምር** | | 100 | **45%** | **30%** | **66.7** | **አማካይ ውጤት** |

**ሠ. መለስተኛ ሙያ ላላቸው ወጣቶች ተጨማሪ የስራ እድል መፍጠር**

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **በግዜያዊ** | | | | | | | |
| 5.1 | ተንዳሆ ሳይት | አፋር | 12,000 | 2,000 | 0 | 0 | የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራው ባለመጀመሩ ቅጥር አልተፈጸመም |
| 5.2 | ጊዳቦ | ኦሮሚያ | 10,000 | 1,000 | 0 | 0 | ›› |
| 5.3 | ጣና በለስ | አማራ | 8,000 | 1,300 | 80 | 6.2 | ›› |
| | **ድምር** | | **22,000** | **9,000** | **80** | **0.9** | |
| **በቋሚ** | | | | | | | |
| 5.3 | ጣና በለስ | አማራ | 800 | 798 | 240 | 30 | ቀድመው ከሰለጠኑት ውስጥ 240 የሚሆኑት ወደ ልማት በመግባታቸው ቋሚ የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡ |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 276.22 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 20.91 ሚሊዮን ብር (7.57 በመቶ) ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮች***

- ❖ **ኦሮሚያ ክልል ጊዳቦ**
  - በዕቅድ ከተያዘውና በወጣቶች ይለማል የከተባለው 5000 ሄክታር መሬት ውስጥ የተገኘው 1800 ብቻ መሆኑ፤
  - በተጨማሪም ይገኛል ከተባለው 1200 ሄክታር በአብዛኛው በእርሻ፣ በመኖሪያ መንደሮች፣ በመቃብር ስፍራዎች እና በግጦሽና በመሣሰሉት አልፎ አልፎ መያዙ፤
  - የሰለጠኑ ወጣቶች ብዛት እና ለጊዜው የተገኘው የመስኖ መሬት አለመመጣጠን
  - በሲሚንቶ አቅርቦት ምክንያት የዘገየው የዋና ካናል ግንባታ አሁን የተጀመረ ቢሆንም ኮንትራክተሩ በሙሉ አቅሙ እየሰራ አለመሆኑ
  - የsecondary canal የኮንትራት አካል ባለመሆኑ የቀጣይ ስራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥሩ መቻላቸው
  - የካምፕ ግንባታው እና መጠጥ ውሃ ቁፋሮ ስራው ከኮንትራት ባሻገር ወደ ተጨባጭ ስራ አለመገባቱ (መዘግየት መኖሩ)፤

❖ **አማራ ክልል ጣና በለስ**

- በእቅድ ተይዞ እንዲለይ ከሚጠበቀው ተጨማሪ የመሬት ልየታ ለማካሄድ በክልሉ በኩል ቃል የተገባ ቢሆንም እስካሁን ተለይቶ የመጣ ተጨማሪ መስኖ ገብ መሬት አለመቅረቡ፡፡
- የካምፕ ግንባታው እና መጠጥ ውሃ ቁፋሮ ስራው ከኮንትራት ባሻገር ወደ ተጨባጭ ስራ አለመገባቱ (መዘግየት መኖሩ)፤

❖ **አፋር ክልል ተንዳሆ**

- ✓ የተመለመሉ ወጣቶችና የተለየ መሬት አለመጣጣም፡፡
- ✓ የምንጣሮ ስራው የተጠናቀቀ ቢሆንም የካናል ጠገና ስራው ውለታ ባመጠናቀቁ ምክንያ ስራው አለመጀመሩ
- ✓ ምንጣሮ በተካሄደባቸው ፒሲ 1 እና ፒሲ 2 ቦታዎች በጽ/ቤታችን በኩል በውል ባልታወቀ መልኩ ለኢንቬስተሮች ተላልፎ መሰጠቱ እና በአሁኑ ሰዓት 3000 ሄ/ር የሚጠጋ መሬት በኢንቬስተሮቹ እየታረሰ መሆኑ፤

❖ **ሲዳማ ክልል ጊዳቦ ክልል**

- ለማህበረሰብ እና ለወጣቶች ተብሎ የተፈቀደ ኮማንድ ለኢንቬስተር የተላለፈ መሆኑ
- በሲዳማ በኩል ወደ ሳይቱ የመግቢያ/የመዳራሻ መንገድ ችግር  መኖሩ
- የመጠጥ ውሃ ችግር መኖሩ በተለይም የከርሰ ምድር ውሃው በፍሎራይድ የተጠቃ መኖሩ
- ለካምፕ ግንባታ እና ለመጠጥ ውሃ  የሚሆን ቦታ ተለይቶ ለኮሚሽኑ ቢላክም ዲዛይን አሰርቶ የኮንትራት ሂደት አለመጀመሩ

**የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች**

- በጣና በለስ የወጣቶች ማረፊያ እና ውሃ አቅርቦት ቀሪ ስራዎችን በፍጥነት ማጠናቀቅ
- በአፋር ክልል ለወጣቶች ተብሎ የመሬት ዝግጅት የተካሄደበትን መሬትን ከኮንትራክተሩ ተረክቦ ቀደም ብሎ ስልጠና ለወሰዱት 211 ወጣቶች ማስረከብ
- በተጨማሪም ከወጣቶች የተረፈውን መሬት እየለማ የሚሄድበትን ስልት መቀየስ እንዲሁም ለ3ኛ ወገን የተላለፉ ፒሲዎችን ጉዳይ በማጥራት ባለቤት መስጠት
- የኦሮሚያ ጊዳቦ የካምፕ ግንባታ እና መጠጥ ውሃ ጉድጓድ ስራን በተያዘለት ግዜ እንዲያልቅ ማድረግ
- በኦሮሚያ በኩል“tumsa” የተባለው የልማት ድርጅት ያቀረበውን ሞዳሊቲ ተፈጻሚነት አረጋግጦ ወደ ስራ የሚገባበትን ሁኔታ መፍጠር
- በተመሳሳይ በሲዳማ በኩል ክልሉ የላከውን መሬት መሰረት በማድረግ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማስጀመር (የግንባታ ስራዎች፣ የመዳረሻ መንገድ ጥገና ስራዎች፣ የወጣቶች ምልመላ እና ስልጠና ስራዎች)፤

- ለሲዳማ ክልል ባለድርሻ አካላት ሊሰጥ የተያዘውን የውይይት መድረክ በማካሄድ ፕሮግራሙን የሚመራ ስቲሪንግ ኮሚቴ ማዋቀር
- በሶማሊ ክልል በፋፈን እና ኩለን ሳይት ላይ ክልሉ ለይቶ የላከውን መሬት መሰረት በማድረግ የመሬት ዝግጅት ስራዎችን ማስጀመር፣

## ሐ. የጥናትና ዲዛይን ፕሮክቶች

## 2.13 የትርካን ግድብና የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኝ ሲሆን ኮሚሽኑ የመጀመሪ ደረጃ ቅድመ ጥናት (Reconnaissance) ለማካሄድ የኮሚሽኑን የባለሙያዎች ቡድን ከክልሉ ውሃ መስኖና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ ባለሙያዎች ጋር በማቀናጀት የዳሰሳ ጥናት ተጀምሯል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን ቀሪ 75 በመቶ የሚሆነውን ሥራ በማከናወን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የኢንሴፕሽን ሪፖርት ዝግጅት፡- 5%
- የፊዚቢሊቲ ጥናት፡- 26%
- የጂኦሎጂና ጂኦቴክኒካል ጥናት፡- 17%
- የዝርዝር ዲዛይን ስራ፡- 27%

**የግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም፡-**

ተርካን የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን የመስኖ ልማት ፕሮጀክት 36 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 12 ከመቶ የተሠራው ሲሆን ይህም 33.3 ከመቶ ተከናውኗል ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት በ2012 መጨረሻ ከነበረበት 25 ከመቶ ወደ 37 ከመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት 9.6 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

## 2.14 የሴጎ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከአርባ-ምንጭ ከተማ 24 ኪ.ሜ. ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ከ5,292 ሄ/ር በላይ በአነስተኛ አርሶ-አደሮች የተያዙ መሬቶችን የሚያለማ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ጥናቱ በ2009 ዓ.ም. የተጠናቀቀ ሲሆን በአሁኑ ወቅት

የጨረታ ስራ ተጠናቆና አሸናፊዉ ተለይቶ ዉል ታስሮ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ከ3160 አባወራ በላይ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይጠበቃል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን ቀሪ 75 በመቶ የሚሆነውን ሥራ በማከናወን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የኢንሴፕሽን ሪፖርት ዝግጅት፡- 5%
- የፊዚቢሊቲ ጥናት፡- 26%
- የጂኦሎጂና ጂኦቴክኒካል ጥናት፡- 17%
- የዝርዝር ዲዛይን ስራ፡- 27%

**የግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም፡-**

ሴጎ የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን በግማሽ ዓመቱ 36 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 27 ከመቶ (የዕቅዱን 75 በመቶ) ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 25 ከመቶ ወደ 52 ከመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት 9.6 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

## 2.15 የሚሌ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት የሚገኘው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዞን 1 በታችኛው አዋሽ አካባቢ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ከሚሌ ከተማ በላይኛው በኩል የሚገደብ ሆኖ በሚሌ ወረዳ የሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎችን ያለማል ተብሎ ይታሰባል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን ቀሪ 75 በመቶ የሚሆነውን ሥራ በማከናወን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የኢንሴፕሽን ሪፖርት ዝግጅት፡- 5%
- የፊዚቢሊቲ ጥናት፡- 26%
- የጂኦሎጂና ጂኦቴክኒካል ጥናት፡- 17%
- የዝርዝር ዲዛይን ስራ፡- 27%

**የግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም፡-**

በግማሽ ዓመቱ ውስጥ የፕሮጀክቱን የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች 36 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ የተመረጠው ቦታ ክልሉ እንዲቀየር ጥያቄ ስላቀረበ አልተከናወነም፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት 9.6 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

## 2.16 የታችኛው በለስ መስኖ ቅድመ አዋጪነት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

የበለስ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚገኝ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ተሰብስቦ የአዋጭነት ጥናት ለመጀመር ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን የመስኖ ቅድመ አዋጪነት ጥናትና ዲዛይን ሥራ 61% በማከናወን በዓመቱ መጨረሻ አጠቃላይ ሥራውን 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የኢንሴፕሽን ሪፖርት ዝግጅት፡- 5%
- የፊዚቢሊቲ ጥናት፡- 26%
- የጂኦሎጂና ጂኦቴክኒካል ጥናት፡- 17%
- የዝርዝር ዲዛይን ስራ፡- 27%

**የግማሽ ዓመቱ ዓመቱ አፈጻጸም፡-**

የታችኛው /አባት/ በለስ የአዋጭነት ጥናትና ዝርዘር ዲዛይን የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን በግማሽ ዓመቱ ውስጥ 27 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 9 ከመቶ (የዕቅዱን 33.3 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ በዚህም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 25 ከመቶ ወደ 48 ከመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት 8.85 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

## 2.17 የጊሎ መስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

የጊሎ መስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚገኝ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ተሰብስቦ የአዋጭነት ጥናት ለመጀመር ከደቡብ ጥናት፤ ዲዛይንና፡ ቁጥጥር ስራዎች ድርጂት ፕሮፖዛል ተጠየቋል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን ቀሪ 80 በመቶ የሚሆነውን ሥራ በማከናወን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የኢንሴፕሽን ሪፖርት ዝግጅት፡- 5%
- የፊዚቢሊቲ ጥናት፡- 26%
- የጂኦሎጂና ጂኦቴክኒካል ጥናት፡- 17%
- የዝርዝር ዲዛይን ስራ፡- 27%

**የግማሽ ዓመቱ ዓመቱ አፈጻጸም፡-**

ጊሎ የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን በግማሽ ዓመቱ ውስጥ 37 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 9 ከመቶ (የዕቅዱን 24.32 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ በዚህም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 20 ከመቶ ወደ 29% ከመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት 9.25 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

## የጥናትና ዲዛይን ቀሪ ሥራዎቻቸው በመከናወን ላይ ያሉ የቦረና እና የሸንሌ ከርሰ ምድር መስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች

- የቦረና የከርሰ-ምድር መስኖ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚገኝ ሲሆን የከርሰ-ምድር ውሃን በመጠቀም ለመስኖ አገልግሎት የሚያውል ፕሮጀክት ነው፡፡
- የሸንሌ መስኖ ጥናትና ዲዛይን በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚገኝ ሲሆን የከርሰ-ምድር ውሃን በመጠቀም ለመስኖ አገልግሎት የሚውል ፕሮጀክት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ 20,000 ሄክታር መሬት ያለማል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ አርብቶ/አርሶ አደሮችንና ወጣቶችን (በወጣቶች የመስኖ ልማት ፕሮጀክት) ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡

**የግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም፡-**

የሸንሌ እና የቦረና የከርሰምድር ውሃ መስኖ ልማት የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን ፕሮጀክቶች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተቀመጠ ምንም ዕቅድ ባይኖርም ነገር ግን በሸንሌ 4 ከመቶ የተከናወነ ሲሆን በቦረና 3 ከመቶ ተከናውኗል፡፡ ይህም ማለት ሸንሌን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 44 ከመቶ ወደ 48 ከመቶ ማድረስ ሲቻል ቦረናን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 43 ከመቶ ወደ 46 ከመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

## 2.18 በዲዛይን ክለሳ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

- የመገጭ መስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን የክለሳ ሥራ የአዋጭነት ጥናቱ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን የዝርዝር ጥናት 10,981 ሄክታር በዕቅድ ተይዞ 7,132 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙ የዕቅዱን 65 ከመቶ ይሆናል፡፡ የማህበራዊ እና የፋይናንሻል አናሊስስ ጥናቶች ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ተልከው ምላሽ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡
- የግልገል አባይ የግድብና መስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን የክለሳ ሥራ በተከሰተው የዲዛይን ችግር ምክንያት የክለሳ ሥራው በዕቅዱ መሠረት ማከናወን አልተቻለም፤ በመሆኑም እስካሁን የሥራው 55 ከመቶ ብቻ ተከናውኗል፡፡

- የጀማ የግድብና መስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን የክለሳ ሥራ እየተሠራ ሲሆን የክለሳ ሥራው 35 ከመቶ ተከናውኗል፡፡
- የገላና ግድብና መስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን የክለሳ ሥራ የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን ሥራው 85 ከመቶ የተከናወነ ሲሆን የማህበራዊ እና የፋይናንሻል አናሊስስ ጥናቶች ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ተልከው ምላሽ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡
- የዳቡስ ግድብና መስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን የክለሳ ሥራ እየተሠራ ሲሆን የክለሳ ሥራው 55 ከመቶ፣
- የጎሎልቻ ግድብና መስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን የክለሳ ሥራ እየተሠራ ሲሆን የክለሳ ሥራው 70 ከመቶ፣
- የብላቴ ግድብና መስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን የክለሳ ሥራ እየተሠራ ሲሆን የክለሳ ሥራው 35 ከመቶ ተከናውኗል፡፡

## 2.19 በ2013 በጀት ዓመት የተጀመሩ የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች

- የሸንፋ የጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማከናወን የአማካሪ ቅጥር ሥራ 100 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ሲሆን በቀጥታ ከአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ጋር የውል ስምምነት የተደረገ በመሆኑ 100% ተከናወኗል፡፡
- የአንገረብ፣ ሞርሞራና ወይጦ የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች አማካሪዎችን ለመቅጠር በግልጽ ጨረታ ሂደት ለማከናወን በታቀደው መሠረት የተጫራቾች ሰነድ በግምገማ ላይ የሚገኝ ሲሆን በአጠቃላይ 70% ተከናወኗል፡፡
- የታችኛው ገናሌ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የቅድመ አዋጭነትና አዋጭነት ጥናት እንዲያከናውን ለኦሮሚያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በቀጥታ የጨረታ ሂደት በመስጠት ድርጅቱ በታዘዘው መሠረት የተሰጠውን ሥራ ቀድሞ የጥናት ቦታውን ለመለየት ከዳይሬክቶሬቱ ሙያተኛ ጋር በመስክ በመገኘት ልየታ በማድረግ በሁለት ክፍል ተከፍሎ እንዲጠና ለአማካሪው በደብዳቤ ተገልጾለታል፡፡ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ በኩል ሎት አንድ በማለት ቅድመ አዋጭነትና አዋጭነት ጥናት 15,000 ሄ/ር እና በሶሜሌ ብ/ክ/መ በኩል ሎት-2 በማለት 40,000 ሄ/ር ዝርዝር ዲዛይን ጥናት እንዲያከናውን ተወስኗል፡፡
- የወይብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ቀደም ሲል በኦሮሚያ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ የቆየ ሲሆን በበጀት ዓመቱ እንደገና በኮሚሽኑ ሙያተኞች ተገምግሞ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ቀድሞ የግድቡ የሚያርፍበት ቦታ ከተጠናበት ወደታች ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈለግ ቴክኒካልና ፋይናንሻል ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ የአሁኑ የኦሮሚያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በደብዳቤ ታዟል፡፡

- የሽፌ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት አስመልክቶ ፕሮጀክቱን ያስጀመረው የደቡብ ክልል መስኖ ልማት አስተዳደር ኤጀንሲ በበጀት ዕጥረት ምክንያት ወደ ኮሚሽኑ ተዛውሮ እንዲከናወን በጠየቀው መሠረት ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ያልተሟላ ሰነድ በመሆኑ ዝውውሩ አልተፈጸመም፤ ለክልሉ መስኖ ልማት አስተዳደር ሰነዱን አሟልተው እንዲያቀርቡና ወደ ጥናቱ መግባት እንዲቻል ትዕዛዝ ተሠጧል፡፡
- በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኘው ብልደሆ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡
- የአድአ በቾ የከርሰምድር መስኖ ልማት ፕሮጀክት ጥናት ለማስጀመር በጨረታው ሂደት የቴክኒካል ግምገማው ያለፈው ተጫራጭ የፋይናንሻል ግምገማው ተከናውኗል፡፡ በግምገማው ውቅት ዕርምት የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ላይ ስምምነት ሃሳብን ለማስቀመጥና ውለታ ለመፈራረም በቀጠሮ ላይ እንገኛለን፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለስምንቱ ፕሮጀክቶች በጥቅል 63.8 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ ተቅዷል፡፡ ሆኖም ዋናው የጥናትና ዲዛይን ሰነዶች ዝግጅት ሥራዎች ባለመጀመራቸው ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- የሚሌ የጥናትና ዲዛይን ሥራ በሁለተኘው ሩብ ዓመት በታቀደው ዕቅድ መሠረት ምንም ያልተከናወነ ሲሆን የተመረጠው የጥናት ቦታ በክልሉ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ችግሩ መፍትሔ እስኪሰጠው ድረስ በመቆየቱ፣ በአካባቢው ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማከናወን የደህንነት ስጋት መኖር፣
- የታችኛው በለስ (አባት በለስ)፤ በአካባቢው ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማከናወን በአካባቢው ያለመረጋጋት ሁኔታ መታየት፤
- በቦረና የከርሰምድር ውሃ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ጥናቱን የሚያከናውነው ድርጅት ጥናቱ የሚከናወንበት ቦታና አካባቢ ለደህንነት ሥጋት አለ ብሎ ማመልከቱ፣
- የጊሎ ጥናትና ዲዛይን ፕሮክትን የሚያከናውነው አማካሪ ድርጅት ግድቡ የሚያርፍበትን የመዳረሻ መንገድ በክልሉ ፈቃደኝነት እያከናወነ ሳለ የአካባቢ ማህበረሰብ ክልከላ መከሰቱ፣
- የግልገል አባይ ግድብ ከአስር ዓመት በፊት በተጠናበት ወቅት የነበረው የመሬት አቀማመጥ በክለሳው ውቅት በጣም ልዩነት በመፈጠሩና የመንገድና የድልድዮችን አቀማመጥ የሚያስቀይር ሆኖ መገኘት፣
- በገላና እና በዳቡስ የጥናትና ዲዛይን ክለሳ ሥራዎች ላይ ግድቡና የመስኖ አውታር በሚያርፍበት ቦታ ላይ የመንገዶች ባለስልጣን መንገዶችን እየገነባ በመሆኑ፤

- የብላቴ ግድብና መስኖ ጥናትና ዲዛይን ሥራን በአካባቢው ገበሬዎች ምክንያት መረጃ መስብሰብ አለመቻል፣

**የተወሰዱ መፍትሔዎች**

- የሚሌ ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማስቀጠል ከክልሉ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት ጥናቱ እንዲጀመር ለአማካሪው ትዕዛዝ ተሰቷል፡፡ የተከሰተው የደህንነት ሥጋት ተፈትቷል፤
- በቦረና የከርሰምድር መስኖ ልማት ፕሮጀክት ወደ አካባቢውና መዳረሻ መንገድ ላይ ይታይ ነበር የታባለው ስጋት በመወገዱ አማካሪው ሥራውን ቀጥሏል፣
- በታችኛው በለስ (አባት በለስ) በአካባቢው የሚታየው አለመረጋጋት አልተፈታም፤
- የጊሎ ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ችግር ከክልሉ መስተዳድር ሃላፊዎች ጋር በመነጋገር ላይ እንገኛለን፡፡
- የግልገል አባይ የተከሰተው የዲዛይን ችግር አማካሪው ባቀረበው ሦስት የመፍትሔ አማራጮች ውስጥ የተሻለውን በመምረጥ ሥራው እንዲቀጥልና በመንገድና በድልድዮች ላይ የሚታየውን ለውጥ ከመንገዶች ባለስልጣን ጋር ለመነጋገር እንደ መፍትሔ ተቀምጧል፡፡
- የገላናና የዳቡስ የመንገዶች ችግር ኮሚሽኑ ለባለስልጣኑ በጻፈው ደብዳቤ መሠረት በውይይት ስምምነት ላይ ተደርሷል፣
- በብላቴ ለተከሰተው ችግር ቀደም ሲል ደብዳቤ ለክልሉና ለወረዳ መስተዳድሮች ተጽፎ ነበር፤ አሁን ግን በአካል በመገኘት ለማነጋገር ታስቧል፣

## ንዑስ ፕሮግራም ሁለት፡ የመስኖ መሠረተ ልማት አስተዳደር ንዑስ ፕሮግራም

### የካፒታልና የመደበኛ ሥራዎች የ6 ወራት አፈጻጸም

**ሀ. ካፒታል ፕሮጀክቶች**

**የመስኖ አውታሮች ጥገና ፕሮጀክቶች፡-** የመስኖ መሰረተ ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመስኖ ልማት ኮሚሽን ውስጥ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ በተደረገው መሠረት በፌዴራል መንግስት የተገነቡና በመገንባት ላይ ያሉ ትላልቅ ግድቦችንና የመስኖ አውታሮችን ለማስተዳደር በአዲስ መልክ ተቋቁሟል፡፡ ይህ ዳሬክቶሬት መደራጀት ያስፈለገበት ዋናው ዓላማ መንግስት ከፍተኛ መዋለ ንዋይ ያፈሰሰባቸው ትላልቅና መካከለኛ የመስኖ ግድቦች የመሰረተ ልማት ውቅሮች በጥናት ወቅት የተቀመጠላቸው የአገልግሎት ዘመን ሳይደርስ ለብልሽት ስለሚጋለጡ በተቀናጀ መልክ ማስተዳደርና አስፈላጊውን ጥገና በወቅቱ ማድረግ በማስፈለጉ ነው፡፡

**የ2013 በጀት ዓመት ግቦች**

- ፈንታሌ መስኖ ፕሮጀክት አስፈላጊው ጥገና ተደርጎለት በድጋሚ ከዚህ በፊት የነበረውን አገልግሎት እንዲሰጥ ዝግጁ ማድረግ፣
- በሶማሊያ ክልላዊ መንግስት የሚገኘውን ጎዴ መስኖ ፕሮጀክት አስፈላጊውን የፊዚካልና ኤሌክትሮ-ሜካኒካል ጥገና አድርጎ በሰው ሀይልና በቁሳቁስ በድጋሚ አደራጅቶ ለስራ ዝግጁ ማድረግ፣
- በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኘው የቆቦጊራና መስኖ ፕሮጀክት የተሟላ ጥገና ተደርጎለት የተለመደውን ስራ እንዲሰራ ማስቻል የመሳሰሉት ናቸው።

**በግማሽ ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራት**

- ❑ የአዋሽ ፈንታሌ መስኖ ጥገና ፕሮጀክት

የዋና መስኖ ቦይ ዋና የደለል መጥረግ እና የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥገና ስራ ማከናውን ሲሆን ይህ ስራ ተጠንኖ ሲያልቅ 2500 ሄክታር የመስኖ መሬት ወደ ልማት የሚያስገባ ሲሆን እስከ ታህሳስ ወር 30 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 30 በመቶ ወይም የዕቅዱን 100 በመቶ ማከናወን ተችሏል።

- ❑ የቆቦ ጊራና መስኖ ጥገና ፕሮጀክትን በተመለከተ

የቆቦ ጊራና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የጥገና ስራ በፕሮጀክቶ እስካሁን በመስኖ የለማው 2800 ሄክታር ሲሆን 800 ሄክታር ተጨማሪ የመስኖ መሬት በማዘጋጀት ወደ 3600 ሄክታር ከፍ ማድረግ ሲሆን የሚከናወኑት ዋና ዋና ስራዎች የኃይል አቅርቦት የሚሆን ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራዎች ( 31 የተለያ መጠን ያላቸው የከርሰ ምድር ውሃ መሳቢያ ፓምፕ እና ተያያዥ ግብዓቶች ግዥ መፈጸም እና 24 የነባር ጉድጓዶች ጠረጋ ማከናወን ሲሆን ለእነዚህ ስራዎች የሚያገለግል የጨረታ ሰነድ በ2 ሎት ተከፋፍሎ ተዘጋጅቷል።

ቡእስከ ታህሳስ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ 35 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 35 በመቶ ወይም የዕቅዱን 100 በመቶ ተከናውኗል።

- ❑ የጎዴ መስኖ ጥገና ፕሮጀክትን በተመለከተ

የጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በጎዴ ዞን በምዕራብ ጎዴ የሚገኝ ከዚህ ውስጥ 4000 ሄክታር ለማልማት ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በዘንድሮ በጀት ዓመት የጥገና ስራ በመጀመር 50 በመቶ ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን የመስኖ ፕሮጀክቱ ለግንባታ የሚሆን መረጃ የሌለውና ይህንን እንዲሰራ ለሶማሌ ጥናት፣ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ጋር የውል ስምምነት ተደርጓል።

እሰከ ታህሳስ ወር 2013 ዓ ም 35 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 በመቶ ወይም የዕቅዱን 42.8 በመቶ ተከናውናል።

**የበጀት አጠቃቀም፡-**

- አዋሽ ፈንታሌ፡- በስድስት ወራት ውስጥ 27 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ ታቅዶ 22.74 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኖ ስራ ላይ ውሏል፡፡
- የቆቦ ጊራና፡- በግማሽ ዓመት ውስጥ 27 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ ታቅዶ 37.38 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኖ ስራ ላይ ውሏል፡፡
- ጎዴ መስኖ ጥገና፡- በስድስት ወራት ውስጥ 54 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ ታቅዶ ነገር ግን ወጪ ሆኖ ስራ ላይ የዋለ ገንዘብ የለም፡፡

## ለ. የመስኖ መሠረተ ልማት አስተዳደር (መደበኛ) ሥራዎች

- ፍትሃዊ የመስኖ ውሃ ስራጭት 50 በመቶ ለማከናውን ታቅዶ 50 ወይም የዕቅዱን 100% ተከናውናል፡፡
- ለዳይሬክቶሬቱ የሚያስፈልገውን ቀሪ የሰው ኃይል ከኮሚሽነሮቹ እና ከሰው ሀብት ልማት ዳሬክቶሬት ጋር በመሆን 100 በመቶ ለማከናወን ታዶ 50 በመቶ ተከናውኗል፡፡
- ግንባታቸው የተጠናቀቁ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ርክክብ በመፈጸም በመስኖ አስተዳደር ስር በማካተት በሰው ሃይልና በቁሳቁስ በማደራጀት የተሙላ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ 100 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም
- በዘንድሮ በጀት ዓመት የመስኖ መሰረተ ልማት ማዕከላትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የክትትልና የግምገማ ስርዓት መዘርጋት 50 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 50 በመቶ ወይም የዕቅዱን 100 በመቶ ተከናውኗል፡፡
- በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ በመስኖ መሰረተ-ልማት ስር የሚተዳደሩ የፊዚካልና ኤሌክትሮ-ሜካኒካል ጥገና የሚያስፈልጋቸው የመስኖ ማዕከላት እንዲጠገኑ ማድረግ 6 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 2 በመቶ ወይም የዕቅዱን 33 በመቶ ተከናውኗል፡፡

**ከዕቅድ ውጪ የተሰሩ ስራዎች**

- በአፋር ክልል ገቢረሱ ዞን በሚገኙ ስድስት/6 ወረዳዎች ማለትም አሚባራ፣ፈንቲአሌ፣ገለአሉ፣ገዋኔ፣ዱለቻ ሀሩካ በሚባሉት ወረዳዎች ውስጥ ባሉ የመስኖ መሰረተ ልማት አውታሮች ላይ በ2012 ዓ/ም የክረምት ወቅት የተከሰተው የጎርፍ አደጋ ያስከተለው ጉዳት መጠንና የተበላሹትና የተጎዱት የመስኖ ውቅሮች (structures) መልሶ ለማቋቋምና ለመጠገን የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የሚያስፈልግ የስራ መጠን እና ለስራው የሚያስፈልግ የዋጋ ግምት በዶክመነትና በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- በዳይሬክቶሬቱ ስር ለሚገኙት ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስራ ማለትም በፕሮጀክት አስተዳደር በግዥና ኮንትራት አስተዳደር የስልጠና ዘርፍ ባለሙያዎች ስልጠናውን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

**በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች**

- ከተፋሰስ ልማት ባለስልጣን የተረከብናቸውን ሰራተኞች ወደ ትክክለኛ ስራ ለማስገባት የቢሮ፣የሰርቪስ መኪና እና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ማጣት፡፡
- በዋናው መ/ቤትም የዳይሬክቶሬቶቹ ሰራተኞች የቢሮ መቀመጫ ቦታ ማጣት፣
- በቆጋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኙ መኪናዎች ሰርቪስ ለማድረግ ረዥም ጊዜ መውሰድ፣
- በቅርንጫፍ ጽቤት የተመደቡ ሰራተኞች ብሶት፣
- የመስኖ ልማት ኮሚሽንና የተፋሰስ ልማት ኮሚሽን የስራ ድርሻ በትክክል መለየት ያለመቻል፣
- የመገጭ ሰራብ መስኖ ልማት የርክክብ ሂደት መጓተት፣

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- የተፋሰስ ልማት ባለስልጣን የቢሮ፣የሰርቪስ መኪና እና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች እንዲያስረክብ ካልሆነም ሰራተኞቹን ወደ እራሱ እንዲመልስ ለማድረግ በደብዳቤ ለሚኒስትሩ ጥያቄ ቀርቧል፡፡
- ቢሮዎች ሲለቀቁ ለሰራተኞች ቅድሚያ እንዲሰጥ ጥያቄ ቀርቧል፡፡
- በቆጋ መስኖ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለሚገኙ መኪናዎች ጥገና የሚያስፈልግ መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ ተጠይቋል፡፡
- በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተመደቡት ሰራተኞች ብሶት ከግምት ውስጥ በማስገባት በቅርብ ቀን ውስጥ መፍትሄ እንደሚያገኙ ማሳወቅ፡፡
- በመስኖ ልማት ኮሚሽንና በተፋሰስ ልማት ባለስልጣን መካከል ያለውን የስራ ሁኔታ የሚለይና ተቋማቱ በየትኛው ስር ለጊዜው እንዲቆዩ ለማድረግ ሃሳብ የሚያቀርብ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሪፖርት ለሚኒስትር መ/ቤቱ አቅርቧል፡፡
- የመገጭ ሰራባ መስኖ ፕሮጀክት ርክክብ ባይደረግም ሰብሉ ውሃ እንዳያጣ የነዳጅ ማቅረብና ውሃ ስርጭት ስራ እተከናወነ ይገኛል፡፡

**ለወደፊቱ ትኩረት የሚሹ ጉዳዬች**

- የማዕከላትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጉዳይ አስቸካይ መፍትሄ ማግኘት አለበት፡፡
- በዘንድሮ በጀት ዓመት ለጥገና የተያዘው ገንዘብ በጣም ትንሽ በመሆኑ በጎርፍ የተጎዳው የመስኖ ቦይዎች እና የፍሳሽ ማስወገጃ ቦይዎች ጥገና ጉዳይ ከመንግስት ጋር በመነጋገር አስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ በአፋር 6 ወረዳዎች የደረሰው ጉዳት የካናሎች ጥገና ለማድረግ ወደ 80 ሚሊዮን ብር ጥገና እንደሚያስፈልገው ባለሙያዎች ሪፖርት ያቀረቡ ሲሆን በማን መጠገን እንዳለበት ግልጽ ውሳኔ ቢያገኝ፡፡

## ንዑስ ፕሮግራም ሶስት፡ የመስኖ ቴክኖሎጂና አቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም

### ሀ. የመስኖ ቴክኖሎጂና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

**መግቢያ**

የመስኖ ውሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) ለሃገሪቷ ከሚሰጠዉ አያሌ ጥቅምና አበርክቶ አንጻር ሲታይና ሲለካ እንዲሁም መልማት ከሚችለዉ የሃገሪቷ አቅም ጋር ሲወዳደር እጅግ በጣም ወደኂላ የቀረና ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ይህ የመስኖ ዉሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) ዘርፍ በሀገሪቷ ላይ የሚከሰተውን ተመላላሽ ድርቅ (Recurrent Drought) ተቋቁሞ በአለም ላይ የተጋረጠዉን የአየር ንብረት ለዉጥ ፈተና (Climate Change) በመመከት የሚጠበቅበትን ዘርፈ ብዙ አስተዋጽዖና ግልጋሎት ለሐገሪቷ ማበርከት እንዲችልና በዉሱንና በአነስተኛ የግዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ወጪ ግብአት በመጠቀም የመስኖ ዉሃ የአቅርቦት (Irrigation Water Supply) ልማቱን አቅሙ የዳበረና በቴክኖሎጂ የታገዘ በማድረግ አገሪቷ ለወጠነችዉ ከፍ ያለ የምጣኔ ሃብት እድገት በፍጥነትና በጥራት ስኬታማና እዉን እንዲሆን ማድረጉ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሚሆን እሙን ነዉ፡፡
በመሆኑም የመስኖ ውሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) ልማትን በተሳለጠና ዉጤታማ በሆነ መንግድ ለማከናወን በዘርፉ ያሉትን ዋና ዋና የስራ ሂደቶችንና የአሰራር ስርአቶችን እንዲሁም ቁልፍ ተግባራትን (Coar Work Processes) ለይቶ ጊዜ ጉልበትና ወጪ ቆጣቢ (Time Cost and Labour Efficient and Effective) እንዲሆኑ አሰራሮችን ማዘመን፤ በቴክኖሎጂ መደገፍና አቅማቸዉን መገንባት እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ነዉ፡፡ እንዲሁም የመስኖ ውሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) የሚተገብሩ አካላትን ለይቶ በክህሎትና በእዉቀት የበቁ ማድረጉ እጅግ ጠቃሚና ጊዜ የማይሰጠዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህንን ጠቅላላ ሀሳብ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችልና አላማዉንና ዝርዝር ተግባራቱን ተንትኖ በማቅረብ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊዉን የገንዘብና የጊዜ ወጪዉን አካቶ ይህ የመስኖ ልማት የቴክኖሎጂና የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡

### ሀ. የካፒታል ፕሮጀክት የግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም

- የመስኖ ልማት ተቋምን መዋቅርና የስራ ፍሰት ያገናዘበ 1 ዘመናዊ የዉስጥ አሰራር (Automated Work Processes) ጥናት 0.6 በመቶ ታቅዶ አፈጻጸሙ 0.12 በማከናወን የእቅዱን 20 በመቶ በአጠቃላይ እስከ ግማሽ አመት ድረስ አፈጻጸሙን 10 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡
- የመስኖ ዘላቂ ልማት እና አስተዳደር በተመለከተ ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት ጋር በአገር አቀፍ ደረጃ ከ4 አውደ ጥናቶች 1.2 በመቶ ለመፈጸም ታቅዶ አፈጻጸሙ 1 በማከናወን የእቅዱን 83.3 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

- የመስኖና ድሬኔጅ ስራዎች 4 የአሰራር ኮድ፣ ስታንዳርድ፣ መመሪያና እና ማንዋል ዝግጅት በ 6 ወራት 2.4 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ አፈጻጸሙ 0.48 ማከናወን ተችሏል፣
- መረጃን በተሟላ፣ በቅልጥፍና እና ከታማኝ ምንጭ ማግኘት የሚያስችል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ብሄራዊ የመስኖ መረጃ ስርዓት 0.3 በመቶ ለመስራት ታቅዶ 0.03 በመቶ ተከናውኗል ።
- መስኩን ከሚደግፋና በመስኩ ላይ ከሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተደረገ የትብብር ስምምነት በቁጥር 1.5 ታቅዶ 0.15 ወይም የእቅዱን 10 በመቶ ተከናውኗል።
- በመስኖ ልማት እውቀት እና ክህሎት ለማሳደግ በፌዴራልና በክልል ለሚሰሩ 150 ሰራተኞች የሐገር ዉስጥና ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 35 ሠራተኞች ስልጠናው ተሰጥቷል።

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 4.0 ሚሊዮን ብር ቢታቀድም ገንዘቡ ወጪ አልተደረገም።

**ለ. የመደበኛ ሥራዎች የግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም፡-**

- የፌደራልና የክልል የመስኖ ልማት ፈጻሚ ተቋማት በአቅም እና በመስኖ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ያሉበትን ሁኔታና ፍላጎቶቻቸዉን የሚያሳይ 1 የክልሎች የቤዝላይን ጥናት ዶኩመንት ስራን በ በ6 ወራት 0.3 ለመስራት ታቅዶ 0.15 በማከናወን የእቅዱን 50 በመቶ ማከናወን ተችሏል።
- የፌደራልና የክልል የመስኖ ልማት ተቋማት አቅማቸዉን ለማጎልበትና በቴክኖሎጂ ለማገዝ የተፈረመ 4 የጋራ መግባቢያ ሰነድ (MOU) ስራን በ 2ኛ ሩብ አመት 1.0 ለመስራት ታቅዶ 0.2 በማከናወን የእቅዱን 20 በመቶ ማከናወን ተችሏል።
- ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ የሐገር ዉስጥና የዉጭ ሐገር ተቋማት ጋር የተፈረመ 4 የጋራ መግባቢያ ሰነድ (MOU) ስራን በ6 ወራት 1.0 ለመስራት ታቅዶ 0.1 በማከናወን የእቅዱን 10 በመቶ ማከናወን ተችሏል።
- በዉስጥ አሰራሮች ጥሩ ተሞክሮ ያላቸዉ ተቋማት እና ከነሱ የተቀሰመ ወደስራ መግባት የሚያስችል 1 ዝርዝር የዉስጥ አሰራር ልምድ ዶኩመንት ስራን በግማሽ አመት 0.3 ለመስራት ታቅዶ 0.03 በማከናወን የእቅዱን 10 በመቶ ተከናውኗል።
- የመስኖ ልማት ተቋምን መዋቅርና የስራ ፍሰትን ያገናዘበ ለሰራተኞች ምቹ ተስማሚ ስራን የሚያበረታታ 1 የስራ አካባቢ ዲዛይን ስራን በ6 ወራት 0.5 ለመስራት ታቅዶ 0.5 በማከናወን የእቅዱን 100 በመቶ ማከናወን ተችሏል።
- ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት ጋር በመስኖ ዘላቂ ልማት እና አስተዳደር ትስስር የሚፈጥር እና ለሚስተዋሉ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጥ 1 አገር አቀፍ አውደ ጥናት የማካሄድ ስራን በ6 ወራት 0.5 ለመስራት ታቅዶ 0.2 በማከናወን የእቅዱን 40 በመቶ ማከናወን ተችሏል።

- በ PPP መልማት የሚችሉ 3 ፕሮጀክቶችን ለይቶ ወደስራ ለማስገባት የተዘጋጀ ቅድመ ሁኔታ የማዘጋጀት ስራን በ6 ወራት 1.0 ለመስራት ታቅዶ 0.1 በማከናወን የእቅዱን 10 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡
- በመስኖ ልማት እውቀት እና ክህሎት ለማሳደግ በፌዴራል ለሚሰሩ 100 ባለሙያዎች የተሰጠ ስልጠና የማከናወን ስራን በ6 ወራት ለ30 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ25 ሰዎች ስልጠና በመስጠት የእቅዱን 83.3 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡
- አመታዊ የፈጻሚዎች ግምገማ የሚያከናዉን እና ለተሻለ አፈጻጸም እውቅና የሚሰጥ ውጤታማ የአሰራር ስርአት የመዘርጋት ስራን በ6 ወራት 0.3 ለመስራት ታቅዶ 0.015 ወይም የእቅዱ 5 በመቶ ተከናውኗል፡፡

**የበጀት አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 2.15 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 275042 ብር ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች**

- የሰዉ ሃይል እጥረት፣
- የቢሮ እጥረት፣
- የተሽከርካሪ እጥረት፣
- ለቴክኖሎጂ ልማትና ማስፋፋትና ለሌሎች ስራዎች ለመስራት የውጭ ምንዛሬ አለመኖር፣
- ወቅታዊ የCOVID 19 ወረርሽኝ መከሰት፣

**ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች**

- የሰዉ ሃይል ቅጥር በአስቸኳይ መፈፀም፣
- ስልጠናዎችንና አዉደጥናቶችን ዉስን ሰዉ ተሳታፊ አድርጎ ማከናወን፣

## ንዑስ ፕሮግራም አራት፡ የአካባቢና ማህበረሰብ ጉዳይ ንዑስ ፕሮግራም

**መግቢያ**

የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ዳይሬክቶሬት የመስኖና ድሬኔጅ ልማቱን ለማሳደግ በሚደረገዉ ጥረት ከመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽኖዎችን በመከላከል ወይም በመቀነስ ካልተቻለም በማካካስ እና በመቆጣጠር እንዲሁም የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋምና በማደራጀት የአርሶ አደሩን የመስኖ ልማት ተጠቃሚነት በማሳደግ የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም ረገድ በ2013 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያከናወነዉን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ቀጥሎ በተመለከተዉ ሁኔታ ያቀርባል፡፡

**ዓላማ፡-** የመስኖና ድሬኔጅ ልማቱን ለማሳደግ በሚደረገዉ ጥረት የሚከሰቱ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽኖዎችን በመከላከል ወይም በመቀነስ ካልተቻለም በማካካስ እና በመቆጣጠር እንዲሁም የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋምና በማደራጀት አርሶ አደሩን በመስኖ ልማት ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

**የ2013 በጀት ዓመት ግቦች**

- ለ80 የልማት ተነሺዎች የካሳ ክፍያ፣ የመልሶ ማቋቋምና የወሰን ማስከበር የድጋፍ ስራ ማከናወን፣
- በተገነቡና በተጠናቀቁ የመስኖ ፕሮጀክቶች 30 የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ማቋቋም እና ድጋፍ ማድረግ፣
- በ2 በተገነቡና እየተገነቡ ባሉ ፕሮጀክቶች የአካባቢ  እና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ በማከናወን ለታዩ ጉድለቶች የማስተካከያ እርምጃዎች መዉሰድ፣
- አራት የአካባቢና ማህበረሰብ የጥናት ዶክመንቶችን ጥራት በመገምገም ፕሮጀክቶቹ በዚሁ ሰነድ መሰረት መተላለፋቸዉን ማረጋገጥ፣

***የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈጻጸም***

- ለኮሚሽኑ፣ የክልል ባለሙያዎች እና የፕሮጀክት አካባቢ ማህብረሰብ ተወካዮች የአቅም ግንባታ ስራ 10 ከመቶ ታቅዶ አፈጻጸሙ 50 ከመቶ፣
- ፕሮጀክቶች ከሚገነቡበት ስፍራ ለሚነሱ የልማት ተነሺዎች በወቅቱ የተከፈለ የካሳ ክፍያ፣ የመልሶ ማቋቋምና የወሰን ማስከበር የድጋፍ ስራን በተመለከተ 10 በመቶ ታቅዶ አፈጻጸሙ 95 በመቶ፣
- በተገነቡና በተጠናቀቁ የመስኖ ፕሮጀክቶች ለተቋቋሙ የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚዎች ማህበራት የተደረጉ ድጋፎችን 12.5 በመቶ ታቅዶ አፈጻጸሙ 50 በመቶ፣
- በተገነቡና እየተገነቡ ባሉ ፕሮጀክቶች የተካሄደ የአካባቢ  እና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ እና የማስተካከያ እርምጃዎች በዕቅዳቸው መሠረት፣
- የአካባቢና ማህበረሰብ የጥናት ዶክመንቶች ጥራትን  ለመገምገም እንዲሁም ፕሮጀክቶች በዚሁ ሰነድ መሰረት መተላለፋቸዉን የማረጋገጥ ስራ በዕቅዱ መሠረት ተከናዉኗል፡፡
- የአካባቢና ማህበረሰብ ጉዳይ ንዑስ ፕሮግራም የግማሽ ዓመት አፈጻጸም 73.9 በመቶ ነው፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለግማሽ ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 1.22 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 1165.80 ብር ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮች***

- የመስክ ተሽከርካሪ እጥረት፣

- በሁሉም ፕሮጀክቶች ባለሞያ መድቦ ለመከታተል የሰዉ ሀይል እጥረት፣

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ**

- በተገኘዉ ትራንስፖርት፣ ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ባለሞያ ጋር በመቀናጀት መስራት፣
- በቢሮ በሚሰሩ ስራዎች የበለጠ አተኩሮ መስራት፣
- ባለዉ የሰዉ ሀይል ሽፍኖ መስራት፣ ቅጥር በአስቸኳይ እንዲፈጸም መስራት በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የ4 ባለሞያዎች ቅጥር እየተጠናቀቀ ይገኛል።

**ለወደፊት መፍትሄ የሚሹ ጉዳዮች**

- በሚመለከተዉ የስራ ክፍል በኩል የመስክ ተሽከርካሪዎች ተሟልተዉ ከዳይሬክቶሬቱ ወደ ፕሮጀክቶች ለሚሰማሩ ባለሞያዎች ተገቢዉ መጠንና ስምሪት በመስጠት ለስራ ማዘጋጀት፣
- ከ2013 ጀምሮ ዳይሬክቶሬቱ ስራዉን የበለጠ ለማከናወንና ዕቅዱን ሙሉ ለሙሉ ለማሳካት ተጨማሪ የሰዉ ሀይል እየተሟላለት ቢሆንም ፀሀፊና የመልዕክት ሰራተኛ ቅጥር ቢፈጸም።
- በእያንዳንዱ ፕሮጀክት የአካባቢና ማህበረሰብ ባለሙያ መድቦ ክትትል ማድረግ፣

## የድጋፍና የክትትል እንዲሁም ከክልሎችና ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ስላለው ቅንጅታዊ አሠራር

➢ **የድጋፍና የክትትል አሠራርን በተመለከተ**

የኮሚሽኑ መ/ቤት በሩብ ዓመቱ ያቀዳቸውን ሥራዎች በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የክልሎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የጋራ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ ተቋሙ የተለያዩ የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓቶችን በመዘርጋት ቀጥሎ በተገለጸው መልኩ ለመተግበር ጥረት አድርጓል:-

- በተቋሙ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች አተገባበር አስመልክቶ በበላይ ሃላፊዎች፣ በፕሮጀክት አስተባባሪዎችና ሌሎች በሚመለከታቸው ባለሙያዎች አማካኝነት ያልተቋረጠ የመስክ ጉብኝትና ክትትል በየጊዜው የሚደረጉ ሲሆን በፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ ለሚከሰቱ ችግሮችም ወቅታዊ ምላሽ በመሰጠት ላይ ይገኛል፣
- በተቋሙና በክልሎች በጋራ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ ከክልሎች፣ከዞኖችና ከወረዳ አስፈፃሚ አመራር አካላት ጋር በቅንጅት የተሠራ ሲሆን ይኸው ቅንጅታዊ አሰራርም ባልተቋረጠ መልኩ በቀጥይ ወራቶች ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፣
- በሩብ ዓመቱ በፕሮጀክቶችና በመደበኛ ሊከናወኑ ከታቀዱ ተግባራት ውስጥ የአንደኛው ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀማቸውንም የበላይ ሃላፊዎችና የተቋሙ ሠራተኞች በተገኙበት በጋራ የመገምገም ስራዎች ተከናውኗል፣

- ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተፈጥሮ ሀብት፣ ማዕድንና መስኖ ዘርፍ ቋሚ ኮሚቴ በ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም ላይ በሰጠው ግብረ መልስ መሠረት በጥንካሬ የቀረቡት ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በድክመት የታዩት በቀጣይ ወራቶች ባለው አፈጻጸም እንዲታረሙ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡
- የሥራ ክፍሎች የሚቀርቡ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ወጥነት እንዲኖራቸው የሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማት/ቴምፕሌት እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
- የዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ መረጃዎችን በማደራጀት በሩብ ዓመቱ ውስጥ ጥያቄ ላቀረቡ መ/ቤቶች የተፈለጉ መረጃዎች ተሰጥተዋል፡፡
- በሚካሄድ የድጋፍ፣ የክትትል እና ግምገማ ስርአት መሠረት ተገልጋይ የሚያነሳቸውን ችግሮች በመለየትና አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ተገልጋዩን የዕቅዱና የትግበራው አካል የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፣
- በፕሮጀክቶች የግንባታ እንቅስቃሴ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ መፍታት እንዲቻል የቴክኒክ እና ስቲሪንግ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ተገቢውን እገዛ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

➢ **ከሌሎች ተቋሞች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አካሄድና አፈጻጸም**

- በኮሚሽኑ አማካኝነት በተለያዩ ቦታዎች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ ከክልሎች፣ከዞኖችና ከወረዳ አስፈፃሚ አካላት ጋር በጋራ በመመካከር፣ በመደጋገፍና ችግሮችን በጋራ የመፍታት ሥራዎች በሩብ ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ሲሆን ይኸው ቅንጅታዊ አሰራርም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፣
- ከተቋራጭ፣ ከአማካሪና ከባለድርሻ አካላት ጋር (ክልል፣ወረዳና ቀበሌ ድረስ ያለውን አመራርና ተጠቃሚ ማህበረሰብ በማሳተፍ) በየሶስት ወሩ የምክክርና የግምገማ መድረክ እየተዘጋጀ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት የሚስተዋሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን የመለየትና ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ በማጠናከር እና አሉታዊ ጎኖችን በማስወገድ በሂደትም ያጋጠሙ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ጥረት ለማድረግ ታቅዷል:: የጋራ ምክክሮች ከፍ ባለ ደረጃ (ክልልና ዞን አመራሮችን ጨምሮ) በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ሲሆን የኮሚሽኑ አመራሮችና ፕሮጀክት አስተባባሪዎች ከአማካሪዉ እና ከተቋራጩ የስራ ኃላፊዎች ጋር በጋራ በመሆን በየወሩ በፕሮጀክቶች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ግምገማ ያካሂዳሉ::
- ከፕላንና ልማት ኮሚሽን ጋር በተቋሙ የአምስት አመት (2013-2017) ዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ በቅንጅትና ተናብቦ የመስራት ሥራዎች ይከናወናሉ፣
- ከውጭ ጉዳይ እና ከገንዘብ ሚ/ር ጋር በልማት ትብብሮችና ፈንድ በማፈላለግ ዙሪያ ስራዎች ተሠርተዋል በቀጣይ ወራትም ይኼው የሚቀጥል ይሆናል፣

- ከምርምር ማዕከላት እና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር እና ቅንጅት በመፍጠር የአጭርና የረዥም ጊዜ የአቅም ግንባታ ስራዎች ለመስራት በመጪው ወራቶች ጥረት ይደረጋል፡፡
- ከአካባቢ፣ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ጋር በአረንጓዴ ልማትና በCRGE ትግበራ ዙሪያ በጋራ ተቀናጅቶና ተናብቦ ለመስራት በመጪው ወራቶች ጥረት ይደረጋል፡፡

## III. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በማጠቃለያ ምዕራፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በሩብ ዓመቱ ሊተገበሩ የታቀዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የማጠቃለያ አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ በከፍተኛና መካከለኛ አመራሩ እና በየዳይሬክቶሬቱ ባሉ ፈፃሚዎች ግምገማ ከተካሄደ በኋላ ወደሚመለከታቸው የበላይ አካላት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡
- በተደረገው ግምገማ መሠረት በአፈፃፀም ወቅት የተከሰቱ ችግሮችን በመለየትና እነዚህም በቀጣይ የሚስተካከሉበትን አሰራርና አካሄድ በማስቀመጥ ያልተከናወኑ ሥራዎችን በዕቅድ ውስጥ አካቶ ለመስራት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡
- ከፕሮጀክቶች ትግበራ ጋር በተያያዘ ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ተግባራት አፈፃፀም ያሉበትን ደረጃ በመገምገም በጥንካሬ የተስተዋሉት ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በድክመት የተለዩትን መቅረፍ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡
- በቀጣይ ወራቶች በዘርፉ የተሻለ ለውጥ ማምጣት እንዲቻል ትኩረት የሚሻቸው ጉዳዮች ተለይተው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

## IV. ወደፊት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ከገንዘብ ሚኒስቴር ለበጀት አመቱ የተፈቀደ በጀት በጊዜ ሰሌዳው መሠረት እንዲለቀቅና በወቅቱ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- የተመደበ በጀትን ለውጤታማና  ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መጠቀም፣
- የተቋሙን የማስፈጸም አቅም ደረጃ ለማሻሻል በብቁ የሰው ኃይልና በማቴሪያል ማሟላት እንዲሁም በዘርፉ ለተሠማሩ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠትና የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው አገራት ጋር የልምድ ልውውጥ እንዲኖራቸው ጥረት ማድረግ፣
- በዘርፉ የጥናት፣ ዲዛይን እና የግንባታ ስራዎች ላይ ለሚሠማሩ የአገር ውስጥ አማካሪዎችና ተቋራጮች አቅም ግንባታ ላይ ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም ልምድ ካላቸው የውጪ ተቋራጮችና አማካሪዎች ጋር በጥምረት (Joint venture) የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ወደግንባታ የሚገቡ ፕሮጀክቶች ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የአዋጪነት ጥናታቸው በባለሙያ ተገምግሞ በትክክል መሬት ላይ መውረድ መቻላቸውንና አሳታፊ መሆናቸውን በመለየት ወደ ስራ የሚገቡበትን ስርዐት መንደፍና መፈጸም፣

- ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ፣በጀትና ጥራት ደረጃ ተከናውነው እንዲጠናቀቁና ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ የሶስትዮሽ አሰራርንና አሳታፊ ዐቅድ ማዘጋጀት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዐትን ማስፈን፣
- ፕሮጀክቶችን በቢሮና በመስክ ያላሰለሰ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሥራዎቻቸው ከዕቅድ ወደኋላ የሚቀሩ ፕሮጀክቶች ካሉ የማካካሻ ዕቅድ በማዘጋጀትና በትርፍ ሰዓትና በሺፍት በመስራት ዕቅዳቸውን እንዲያሳኩ ማድረግ፣
- በየፕሮጀክቱ የተጠቃሚ ዜጎች፣ የህዝብ አመራርና የፕሮጀክት ተዋንያን የጋራ የመሠረተ ልማት ኮሚቴ በማቋቋም ሥራዎች የሚገመገሙበትና ሁሉም አካል ለችግሩ መፍትሄ የሚሆንበትን ሥርዐት መዘርጋት፣
- ኮሚሽኑ በሚገነባቸው የመስኖ አውታሮች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ወይም መሰል የማህበራዊ ችግሮች እንዳይከሰቱ በመሠረተ ልማቱ ግንባታ ጥቅምና ፋይዳ ዙሪያ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልል፣ ዞንና ወረዳ አመራሮች እና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መስራትና እገዛና ትብብር እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- አካባቢው ላይ የሚደረጉ ያለአግባብ ስራ ማስቆም፣ የመሰረተ ልማት ስራዎችን ማፍረስና ስርቆት የመሳሰሉት ችግሮች እንዳይከሰቱ ከጸጥታ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት፣
- የመሬት አቅርቦትና የግንባታ ግብዐት የሚመረትባቸውን ቦታዎች በሚፈለገው ፍጥነት ለተቋራጮች እንዲፈቀድ ማድረግ፣
- ለልማት ተነሺዎች ተገቢውን ካሣ በወቅቱ ለመክፈል ተሻሽሎ የወጣው የካሣ አዋጅ መመሪያ በፍጥነት ወደ ታች እንዲወርድ ግፊት ማድረግ፣
- የግሉ ዘርፍ በመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ላይ በስፋት እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እና ድጋፍ ማድረግ
- የሚነደፉ የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ስርዓተ ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግና እንደ አግባቡ በሚገነቡ ተቋማት ሴቶች ከፍተኛ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ላይ ትኩረት መስጠት
- በፕሮጀክቶች የሚከናወኑ የግንባታ ተግባራትን እንደፕሮጀክቶቹ ሁኔታ በመከፋፈል ከአንድ በላይ በሆኑ ተቋራጮች ማከናወን፣
- ነባር የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን አስፈላጊውን ርብርብ በማድረግ አጠናቆ ወደ ልማት መስገባት፣
- አዲስ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች ዋናው ስራ ከመጀመሩ በፊት ግንባታ የሚካሄድበትን የመሬት አቅርቦት ጉዳይ አስቀድሞ ማጠናቀቅ፣
- በየፕሮጀክቱ የግብአቶች እጥረት (የሰው ሃይል፣ ማሽነሪ፣ ወዘተ) እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትል ማድረግ፣

- በበጀት ዓመቱ የግንባታ ስራ የማይሰራበትን መሬት /Working corridor/ ለተማሩ ወጣቶች የመስኖ እርሻ እንዲውል ማድረግ፣
- ለወጣቶች መስኖ ልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ባለድርሻዎችን በማስተባበርና በመቀናጀት መፈፀም፣
- የወጣቶች መስኖ ከሂደት /process/ ወጥቶ በተጨባጭ ወደ ስራ የሚገባበትን አቅጣጫ ማስቀመጥ፣
- በመስኖ ቴክኖሎጂ አርሶ አደሩ እና የግል ባለሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን እስከ ታችኛው አስተዳደር በጋራ መስራት፣
- ተቋሙ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ግንባታ እና መጠኑ ከፍተኛ የሆነ በጀት የሚያንቀሳቅስ ቢሆንም የተመደበለት የደመወዝ ስኬል ተመሳሳይ ሥራ ከሚያከናውኑ ድርጅቶች ያነሰ በመሆኑ ሳሉትና ሌሎች ብቁ ባለሙያዎችን ከገበያ ላይ መቅጠር እንዲቻል የተቋሙ የደመወዝ ስኬል የሚስተካከልበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በሁሉም ደረጃ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችም ሆኑ መረጃዎች በሚፈለገው ጥራት፣ወቅት፣አይነት ማግኘት እንዲያስችል የተጠናከረ የድጋፍ፣ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ስርዓትን በመዘርጋት የሚተገበር ይሆናል።

# አባሪ ሠንጠረዦች፡

# የፕሮግራም በጀት እና የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ማቅረቢያ ቅፆች